እንኳን ወደ ጀርመን በስላም መጣችሁ

የሂወት ጉዞ መምርያ ለአቅመ ኣዳም ላልደርሱ ወጣቶች

ሰላም (Hallo)

እዚህ ጀርመን አገር ብቻችሁን መጥታችኋል፤ በእርግጥ ብዙ ጥያቄዎች ይኖራችኋል። ይህ አጭር መጽሄት ጥያቄዎቻችሁን ለመመለስ ሊረዳችሁ እና ማንን እንደምትጠይቁ መግለጫ ሊሰጣችሁ ይችላል። እዚህ ሊያጋጥሟችሁ ለሚችሉ ነገሮችና ምን ምን መብቶችም እንዳላችሁ እንድታውቁ ልንረዳችሁ እንፈልጋለን። እኛም እንደናንተው ተመሳሳይ ሁኔታን ያሳለፍንና የተደራጀን ወጣቶች ነን። እዚህ አገር እናንተን ለመርዳት የተደራጁና የተዘጋጁ ብዙ ሰዎች አሉ። ስለሆነም ብቻችሁ አይደላችሁም እንላችኋለን!

ይህ መጽሄት ስድስት ክፍሎች አሉት፤ የሚቀጥለው ገጽ ላይ የአርስቶች ዝርዝር ሰፍሯል። ከዚያ ቀጥሎ ያለው ገጽ ደግሞ ጀርመን አገር ከገባችሁ ከመጀመሪያዎቹ ቀናት ጀምሮ ሊያጋጥሟችሁ የሚችሉ ነገሮች፣ ምን ዐይነት ዕድሎችና መብቶች እንዳላችሁ፣ ከየትኞቹ የመንግስት መስሪያቤቶች ከነማን ሰዎች ጋር መገናኘት እንዳለባችሁ እናብራራላችኋለን። የተወሳሰቡ ጽንሰ-ሃሳቦችና ቃላቶች በጽሁፉ ውስጥ ለየት ባለ ቀለም ተጽፈው በስድስተኛው ክፍል አጠር ባለ መልክ ይገለጻሉ።

ስለእኛ ለማወቅ ከፈለጋችሁ፣ መጽሄቱ ውስጥ ማግኘት ትችላላችሁ። የሚያስፈልጓችሁን መረጃዎች (Information) በሙሉ እንደምታገኙ ተስፋ እያደረግን ለወደፊት ዕድላችሁ መልካሙን እንመኝላችኋለን!

ይዘት

ክፍል 1፤ እንኳን ወደ ጀርመን በደህና መጣችሁ - እዚህ መምጣታችሁ ጥሩ ነው! — 1
መድረስ/መምጣት
መብቶቻችን ምንድን ናቸው?
እዚህ አገር ምን ህጎች አሉ?

ክፍል 2፤ የመጀመሪያው እርምጃ- በመጀመሪያ ምን ይፈጠራል? — 7
የወጣቶች ተቋም ምን ማለት ነው? ስራውስ ምንድነው?
በመጀመሪያ የደረስንበት ከተማ መቆየት እንችላለን?
ዕድሜያችን ይህን ያህል ለምን አስፈለገ ?
ዕድሜንስ መገመት ማለት ምን ማለት ነው?
የሴት ወይም የወንድ ሞግዚቶቻችን ምን ያደርጉልናል?
እኛን የሚንከባከቡ ምን ያደርጉልናል?
የት ነው የምንኖረው?
ብንታመም ምን ማድረግ እንችላለን?

ክፍል 3 ፤ መኖሪያ - ጀርመን አገር ልንቆይ እንችላለን ወይ? — 19
የትኞቹ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ናቸው ለእኛ አስፈላጊዎች?
አማራጭ 1፤ ጥገኝነት የመጠየቅ መብት አላችሁ!
አማራጭ 2፤ ጥገኝነት ሳታመለክቱ ለመቆየት የሚኖሯችሁ መብቶች!
የጥገኝነት ማመልከቻው ተቀባይነት ካላገኘ፤ የአገር መልቀቅ ጥሪና አስገድዶ ማስወጣትን የሚመለከት ጉዳይ
ቤተሰቦቻችንን ወደ ጀርመን ማስመጣት እንችላለን?
የደብሊን ሂደት ማለት ምን ማለት ነው?

ክፍል 4፤ ትምህርት - አሁን አንድ ነገር መማር — 31
ወዲያውኑ ትምህርትቤት መግባት እንችላለን?
የሞያ ትምህርት/ስልጠና ማለት ምን ማለት ነው? ማድረግ እንችላለን?
የመልቀቂያ ፈተና ምንድን ነው? ዩንቨርስቲ መማር ለማን ነው የሚፈቀደው?
ዕድሜያችን ከ18 ዓመት በታች ከሆነ መስራት ይፈቀድልናል?
የሞያ ስልጠናችንና የዩኒቨርሲቲ ትምህርታችንን እንዴት መክፈል እንችላለን?

ክፍል 5፤ ለእለታዊ ኑሮ የሚሆን ምክር — 41
የባንክ ሂሳብ (አካውንት) መክፈት እንችላለን?
በትርፍ ጊዜያችን ምን ማድረግ እንችላለን?
ሌላ አገር ወይም ሌላ ከተማ መሄድ ይፈቅድልናል?
ቤት ተከራይተን ብቻችንን መኖር እንችላለን?
መኪና መንዳት ይፈቀድልናል?
የት ነው እርዳታ ማግኘት የምንችለው?

ክፍል 6፤ ጽንሰሃሳቦችን/ቃላቶችን መግለጽ — 47

መድረስ/ መምጣት

ጀርመን አገር ስትገቡ ምናልባት ምን ማድረግ እንዳለባችሁ አታውቁም ይሆናል። ምናልባት ዕርዳታ ያስፈልጋችሁ ይሆናል። የሚረዷችሁ የተለያዩ የመንግስት ተቋማትና (Behörde) ሰዎች ዘንድ፣ ለምሳሌ ወጣቶችን የሚንከባከብ መስሪያቤትና ፖሊስ ጋ እራሳችሁን ማስተዋወቅ ይኖርባችኋል። የምትኖሩበትም ቦታ እራሳችሁን ለሁሉም ማስተዋወቅ አለባችሁ። የምትኖሩበት ቦታ እናንተን የሚንከባከቧችሁ(Betreuer/in) ሰዎች ይመደቡላችኋል። እነሱ በሚያጋጥሟችሁ ችግሮችና የእለታዊ ኑሯችሁ ይረዷችኋል። ለምሳሌ ከሃኪም ጋር ቀጠሮ ካላችሁና ወደ ገበያ ለመሄድ ከፈለጋችሁ ይወስዷችኋል። ወደ ትምህርትቤት እንድትሄዱ፣ እንድታጠኑና የትምህርትቤት ስራም እንድትሰሩ ያበረታታሉ። ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላም ስለምትኖሩበት ከተማ ያስረዷችኋል፤ መረጃዎችም ይሰጧችኋል፤ ስለሚፈቀዱላችሁና ስለማይፈቀዱላችሁ ነገሮች ያስረዷችኋል። ለምሳሌ ያለቲኬት በአውቶብስም ሆነ በባቡር መሄድ አይፈቀድላችሁም። ሌላው በጣም አስፈላጊ ምክር መስረቅና ካለስራ ፈቃድ መስራት እንደማይፈቀድላችሁ ነ።

ጀርመን አገር ለሁሉም ነገር ህግ አለ። ለነዚህም የተለያዩ የህግ መጽሃፍቶች አሉ። ለምሳሌ፤ የወንጀል ሕግ፣ የጥገኝነት መብት ሕግ፣ ልጆችንና ወጣቶችን ድጋፍ የሚሰጥ ሕግ (Strafrecht, Asylrecht, Kinder- und Jugendhilfegesetzt) እና ሌሎችም አሉ። ጀርመን ዲሞክራሲ የሰፈነበት አገር ሲሆን፣ ማንኛውም ዜጋ መብቱንና ግዴታውን መጥበቅ አለበት፤ ማንኛውም ሰው ብዙ መብቶች አሉት፤ ይሁንና ግን ብዙ ደንቦችም አሉ።

እንኳን ወደ ጀርመን በሰላም መጣችሁ

እዚህ መምጣታችሁ ጥሩ ነው!

ስለጀርመን አንዳንድ ተጨማሪ መረጃዎች ፤
የጀርመን ሙሉ ስም ፌደራል ሪፖብሊክ ጀርመን ነው። „Bundes“ የሚለው ቃል ትርጉሙ ጀርመን የብዙ ክፍለ-ሃገራት ውህደት/ፌደረሽን ማለት ነው። ለምሳሌ እንደ ባየርን፣ ኖርድራይን ቬስትፋለን ወይም ደግሞ በርሊን። ጠቅላላውን ጀርመን ከሚወል ፌደራላዊ መንግስት ከመኖሩም ሌላ፣ 16 ክፍለ-ሃገራት የየራሳቸው ፌደራላዊ መንግስት (=Landesregierung) አላቸው። መንግስት ያገሩ የፖለቲካ ሃላፊ ነው። በብዙ ነገር ላይ የየክፍለ-ሃገራቱ መንግስታት ከጠቅላላ ኣገር ፈደርላዊ መንግስት ጥገኞች ኣይደለኡም።ለምሳሌ ስደተኞች የትና እንዴት እንደሚኖሩ እና ትምህርትቤት ጉዳይ። ስለሆነም ለስደተኞች የመጠጊያ ወይም የመኖሪያ ቦታ መስጠትን በሚመለከትና፣ ማን መቼና የት ትምህርትቤት መግባት እንዳለበት በየክፍለ-ሃገራቱ መሀከል ትልቅ ልዩነት አለ። ስለዚህም ወጣት ስደተኞች በመጀመሪያ ጀርመን ኣገር በሚኖሩበት ወቅት የተለያየ ልምድ/ተሞክሮ ያካብታሉ

የእኔ መብቶች ምንድን ናቸው ?

ጀርመን አገር ውስጥ የሰው ልጅ መብት የተጠበቀ ነው። ማንኛውም ሰው የራሱን ሃሳብ የመግለጽ፣ የሃይማኖት እና የፖለቲካ አቋም የመከተል መብት ሲኖረው ስለነዚህም ነገሮች በነፃነት የመናገር መብት አለው።

ጀርመን አገር የፖለቲካ ጥገኝነት (Asyl) ማመልከት ይቻላል። ሁሉም ሰዎች በጦርነት ምክንያት አገራቸውን ጥለው እንዲወጡ የተገደዱ ጥገኝነት ማመልከት ይችላሉ። ጀርመን አገር ተቀባይነት ያላቸው ሌሎች የስደት ምክንያቶችም አሉ። ለምሳሌ በወጣት ሴቶች ላይ የሚደርስ ግፍ የተሞላበት የግብረ-ስጋ ግኙኝነት፣ ግብረሰዶማዊነት፣ ያለፈቃድ የሚፈጸም ጋብቻ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ምክንያቶች ናቸው።

ስለእናንተ የሚደረጉትን ነገሮች ሁሉ የማወቅ መብት አላችሁ። በብዙ ሁኔታዎች ስለሚባለውና እናንተ ስለምትናገሩት እንዲተርጉምላችሁ አስተርጓሚ (Dolmetscher/in) ይመደቡላችኋል። ለኑሮ ምን እንደሚያስፈልጋችሁና እንደማይስፈልጋችሁ የመናገር መብትም አላችሁ። የእናንተን ሃሳብና ፍላጎቶች ሁሉ መጠበቅ አለባቸው።

እንደ ታዳጊና ወጣት ልጆች በጀርመን አገር ያሏችሁ መብቶች የሚከተለውን ይመስላሉ፤

ከወላጆቻችሁ ጋር የማትኖሩ ከሆነ እና ጀርመን አገር ተስዳችሁ ከመጣችሁ፤ በመንግስትና በመንግስት ጽህፈት ቤቶች ልዩ እንክብካቤ የማግኘት መብት አላችሁ።

ትምህርትቤት የመሄድ መብት አላችሁ።



ህክምና የማግኘት መብት አላችሁ።



የሰላምና የዕረፍት ጊዜ የማግኘት መብት አላችሁ። በግዴታ እንድትሰሩ አይፈቀድም።

ያለወላጆቻችሁ ከመጣችሁ በወጣቶች ተቋም በኩል ማንኛውንም ዕርዳታ (Inobhutnahme) የማግኘት መብት አላችሁ። የወጣቶች ተቋም ልክ እንደወላጆቻችሁ/ አስዳጊዎቻችሁ ማንኛውንም እንክብካቤ የማድረግ ግዴታ አለበት።

እናንተን የሚመለከት
በማንኛውም ነገር የሚወክላችሁ ሞግዚት (Vormund/Vormundin) የማግኘት መብት አላችሁ።

ደህንነታችሁ እንዲጠበቅና ያላችሁበት አዲስ ሁኔታ ጋር እንድትለማመዱ፤ የልጆችና የወጣቶች ተንከባካቢዎች ያሉበት የመኖርያ ቦታ የመመደብ መብት አላችሁ።አለኩም።

ከወላጆቻችሁ ጋር የመኖር መብት አላችሁ። ወላጆቻችሁ፣ ታላላቅ ወንድሞቻችሁ፣ ወይም የቅርብ ዘመዶቻችሁ ሌላ የአውሮፓ አንድነት አገር የሚኖሩ ከሆነ እነሱ ጋር የመሄድ መብት አላችሁ።

እናንተን
የሚመለከት ውሳኔ ከመንግስት መስሪያቤት
(Behörden) ከመጣላችሁ እና በውሳኔው የማትስማሙ ከሆነ የመክሰስ (Klage) ወይም ይግባኝ (Widerspruch) የማለት መብት አላችሁ። ይህንን በሚመለከት የመንግስት መስሪያቤቱ ሰራተኞችና ድርጅቶች (Organisationen) መረጃ ሊሰጧችሁ ይገባል።

ይህ ሁሉ ነገር አስቸጋሪ ይመስላል። ይሁንና ስለእናንተ ምን እንደሚደረግ የማወቅና በማንኛውም ውሳኔ ላይ የመካፈል መብት አላችሁ። ሕግን የሚመለከት ነገር ካጋጠማችሁ ጠበቃ ጉዳዩን እንዲያስፈጽሙላችሁ መስጠት ትችላላችሁ፤ ነገር ግን ብዙ ገንዘብ ይጠይቃል። ትንሽ ገንዘብ ላላቸው ሰዎች፤ ጀርመን አገር በነጻ ሊረዱ የሚችሉ አማካሪ ጽህፈትቤት አሉ።

ጀርመን አገር ምን ዐይነት ደንቦች አሉ ?

ጀርመን አገር ብዙ ዐይነት ደንቦች አሉ። ሁሉም ነገር የሚሰራው በህግና በደንብ ነው። እድሜያችሁ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ ወላጆቻችሁ፣ አሊያም የወጣቶች ተቋም (Das Jugendamt) ስለእናንተ ጉዳይ ይወስናል። ከ18 ዓመት በታች ከሆናችሁ ማጨስ አይፈቀድም። በተጨማሪም የመንጃ ፈቃድ ማውጣት የምትችሉት 18 ዓመት ከሞላችሁ በኋላ ነው። የመታወቂያ ወረቀታችሁን ሁልጊዜ መያዝ አለባችሁ። በአውቶቡስ፣ በባቡር፣ በትራምና በመሳሰሉት የህዝብ ማመላለሻዎች ለመጓጓዝ ከፈለጋችሁ ሁልግዜ ትኬት ያስፈልጋችኋል፤ ጉዞ ከመጀመራችሁ በፊት መጀመሪያ ትኬት መግዛት ይኖርባችኋል። ለመጀመሪያ ጊዜ ጀርመን አገር እንደ ስደተኛ ከገባችሁ ትመዘገባላችሁ። ከዚያ በኋላ የት ቦታ መኖር እንደሚፈቀድላችሁ ይወሰናል። የሚመለከተው መስሪያቤት ስትሄዱ ሁልጊዜ ወረፋ መጠበቅ ያስፈልጋል። የሚመለከተው መስሪያቤት እንደደረሳችሁ በመጀመሪያ የወርፋ ቁጥር መውሰድና ወረፋ እስኪደርሳችሁ ድረስ መጠበቅ ያስፈልጋል። ያም ሆኖ ሁልጊዜ በሰዓታችሁ መገኘት አስፈላጊ ነው። አንድ ነገር ለምድረግ የሚፈቀድ መሆኑን ካላወቃችሁ የሚንከባከቧችሁንና (Betreuer/ Betreuerin) ሞግዚቶቻችሁን (Vormund/Vormundin) መጠየቅ ትችላላችሁ።

ጀርመን የቢሮክራሲ አገር ነው። ይህም ማለት ሁሉ ነገር ደንብን ተከትሎ ነው የሚሰራው። መንግስት
ለሁሉም አስፈላጊ ለሆኑት የስራ ሂደቶች ኃላፊነትን ጠንቅቀው ለሚያውቁ ሰራተኞች የስራውን ሂደት ወስኖ
በጥንቃቄ እንደሚሰሩና እንደሚመዘገቡ ያደርጋል። ለስራውም ሂደት ወረቀቶች፣ ፊርማና ማህተም በጣም አስፈላጊ ናቸው።
ስለዚህ በሙሉ ዶክመንታችሁ በጥንቃቄ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ሰርትፍኬቶቻችሁ (Zeugnisse)፣
ከኢሚግሬሽን ቢሮ የሚሰጣችሁን ወረቀቶች። ወረቀቶቻችሁ በሙሉ በጣም ጠቃሚ ስለሆኑ አባዝቶ (ኮፒ ኣድርጎ) ማስቀመጡ ጥሩ ነው።
„ትዕግስት ሁልጊዜ ከባድ ነው። ሆኖም ግን መታገስ አለብን።“

የወጣቶች ተቋም (Jugendamt) ምን ማለት ነው ? ስራውስ ምንድነው?

ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች ያለ ወላጅ ወይም ያለ አሳዳጊ (Sorgeberechtigte) ወደ ጀርመን አገር ከመጡ የወጣቶች ተቋም ለእነዚህ ወጣቶች ኃላፊነት ይወስዳል። ልእናንተም ማለት ነው። ይህ ማለት እናንተ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንድትገኙ አስፈላጊውን ነገር ያደርጋል። የወጣቶች ተቋም የመንግስት መስሪያ ቤት (Behörde) ሲሆን፣ በየወረዳዎችና በየከተማዎች ይገኛል።

ይህ ተቋም ለህይወታችሁ ዋስትና አስተማማኝ ቦታ እንድትኖሩ ከማድረጉም ሌላ ለኑሮ የሚያስፈልጉ እንደምግብ፣ ልብስና የጤና ጥበቃ እንድታገኙ ያደርጋል ይህን የመሰለ እንክብካቤ (Inobhutnahme) ይባላል።

በተጨማሪም የሚንከባከቧችሁ ሰዎች ይኖራሉ። በየስድስት ወሩ የዕርዳታ ዕቅድ ንግግር (Hilfeplangespräch) በእናንተና በወጣቶች ተቋም መሀከል ይደረጋል። የዚህም ንግግር አስፈላጊነት አሁን ያላችሁበትና ወደፊት መሆን ያለበት ሁኔታ ለመነጋገር ነው።

ሞግዚት ከሌላችሁ እና እንዲሁም መጠጊያ የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ የወጣቶች ተቋም ለእናንተ የጥገኝነት ማመልከቻ ሊጽፍና ሊያስገባ ይችላል። እናንተ ለዚህ ነገር ፍላጎት እንዳላችሁ ተቋሙ ማወቅ አለበት። የወጣቶችም ተቋም እናንተን የሚንከባከቡና እንደሞግዚት ሆነውም ሁሉንም ነገር የሚያደርጉላችሁ ሰዎች ለመፈለግ ጥረት ያደርጋል። ሞግዚቶች ህግ ነክ የሆኑ ነገሮችን የሚያስፈጽሙ ሲሆኑ፣ ተንከባካቢዎች ደግሞ ለኑሮ የሚያስፈልጉ እለታዊ ነገሮችን ለምስፈጸም የሚረዱ ናቸው።

18 ዓመት እስካልሞላችሁ ድረስ የወጣቶች ተቋም ገንዘብ ይከፍልላችኋል። ተቋሙ ለመኖሪያ ቤት፣ ለምግብ እና አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች በሙሉ ይከፍላል። በተጨማሪም ለሚያስፈልጓችሁ ነገሮች መግዢያ የሚሆን የኪስ ገንዘብ ይሰጣችኋል።

ከመጀመሪያውኑ ጀምሮ የወጣቶች ተቋም የእናንተን የወደፊት ሁኔታ በሚመለከት የሚያደርገው ማጣራት Clearing ይባላል። ምናልባት በመጀመሪያው ወቅት ማጣሪያ „Clearingsstelle“ ተብሎ በሚጠራው ቦታ እንድትኖሩ ይደርግ ይሆናል። ይህ ጉዳይ ግን እንደሁኔታው በጣም ይለያያል።

የመጀመሪያው እርምጃ
በመጀመሪያው ወቅት ምን ይፈጠራል?

በመጀመሪያ የደረስኩበት ከተማ መቆየት እችላለሁ?

ምናልባት መጀመሪያ የደረሳችሁበት ከተማ የወጣቶች ተቋም ለማኖሪያ የሚሆነው ተጨማሪ ቦታ ላይኖረው ይችላል፤ ሌላ አካባቢ ወይም መንደር ክፍት ቦታ ሊኖር ይችላል። ስለሆነም የግዴታ ሌላ ቦታ መሄድ ይኖርባችኋል& ትቀዘራላችሁ። ይህም ማከፋፈል ወይም መመደብ ይባላል።

በመጀመሪያ ደረጃ የት ቦታ እንዳለ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። እስከዚያ ጊዜ ድረስ በመጀመሪያ ያረፋችሁበት የወጣቶች ተቋም ጋር ትቆያላችሁ። ይህም ጊዚያዊ ማስጠጊያ (vorläufige Inobhutnahme) ተብሎ ሲጠራ፣ ቢበዛ አንድ ወር ብቻ ነው እዚያ የምትኖሩት በዚህ ጊዜ ውስጥ የወጣቶቹ ተቋም የት ቦታ መሄድ እንደሚኖርባችሁ ያጣራል። ከተቋሙ ጋር ለመነጋገር መብት አላችሁ። ለምሳሌ ከሌሎች ወጣቶች ወይም እህትማማቾች/ ወንድማማቾች ጋር በጉዞ ወቅት አንድ ላይ ከነበራችሁ ከማን ጋር ለመቆየት ወይም ለመኖር እንደምትፈልጉ መናገር ትችላላችሁ። በጥሩ ሁኒታ ላይ ካልሆናችሁ፣ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ የማትፈል ከሆነ ምናልባት ሌላ ቦታ መሄድ ላይኖርባችሁ ይችላ። ሌላ የጀርመን ከተማ ወይም ሌላ የአውሮፓ አገር ዘመዶች ካሏችሁና እዚያ ለመሄድ ከፈለጋችሁ መናገር ትችላላችሁ። ይህ ጉዳይ በብዛት በቶሎ የሚያልቅ ነገር አይደለም። ምን እንደምትፈልጉ ከተንከባካቢያችሁ ጋር መነጋገር ትችላላችሁ። የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው ግን የወጣቶቹ ተቋም ነው።

ለምድን ነው ዕድሜ ይህን ያህል አስፈላጊ የሚሆነው፣ ዕድሜንስ መገመት ማለት ምን ማለት ነው ?

ጀርመን አገር ዕድሜ በጣም አስፈላጊ ነው። ጀርመን አገር ከደረሳችሁ በኋላ የወጣቶች ተቋም፣ ሞግዚቶች፣ የኢምግሬሽን ቢሮና፣ ፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ጽህፈት ቤት (BAMF) ዕድሜያችሁን ማወቅ ይፈልጋሉ። የዕድሜ ጉዳይ ለእናንተ መኖሪያ ቦታ ለመፈለግና የጥገኝነት ማመልከቻ ለማስገባትና ለሂደቱ (Asyslverfahren) በጣም አስፈላጊ ነው።

ነገር ግን በስደት ጉዟቹ ላ መታወቂያም(Identität) ሆነ ሌላ ማረጋገጫ ወርቀ ከሌለላችሁ ዕድሜያችሁን ለማወቅ በጣም ያስቸግራል። በዚህ ምክንያት ኣንድ ኣንድ ግዜ ዕድሜያችሁ ላይታመን ይችላል። ከአገራችሁ የመታወቂያ/የማረጋገጫ ወረቀት ማስመጣት የማትችሉ ከሆነ ወይም በፍጹም ማግኝት የማይቻል ከሆነ ዕድሜያችሁን በህክምና መንገድ ለመገመት ይሞከራል

በአንድ ኣንዶቹ የጀርመን ክፍለ-ሃገራት ሃኪም ጋር ሄዳችሁ ምርመራ እንድታደርጉ ይመክሯችኋል። ሃኪሞቹ፣ ለምሳሌ ሰውነትን፣ አጥንትን፣ እጆችንና ጥርሶችን ከመረመሩ በኋላ ዕድሜያችሁ ስንት እንደሆነ ይወስናሉ። በእያንዳንዱ ቀጠሮ ጊዜ ተንከባካቢዎቻችሁ ወይም ሞግዚቶቻችሁ አብረዋችሁ ብሄዱ ይመረጣ። ሌላ የዕድሜ መገመቻ ዘዴ (Alterseinschätzung) ወይም ኣማራጭ ካለም መረዳት በምትችሉት ቋንቋ ሊነገራችሁ ይገባል እንደጾታችሁ የሴት ወይም የወንድ ሃኪም የመምረጥ መብት አላችሁ። ሴት ልጅ በሴት ሃኪም፣ ወንድ ልጅ ደግሞ በወንድ ሃኪም ይመረመራል።

አልፎ አልፎ ሳታውቁት ዕድሜያችሁ ይገመታል። አንድ ነገር ስትፈርሙ ሁልጊዜ መጠንቀቅ ያለባችሁ ነገር ዕድሜያችሁ በትክክል መመዝገቡን ነው። በምርመራው መሰረት ዕድሜያችሁ 18 ዐመት ወይንም ከዚያ በላይ መሆኑ ከተገመተ ከጠበቃችሁ ጋር መነጋገር ትችላላችሁ፤ ወይም ደግሞ ከሌላ ባለሞያ (ለምሳሌ ምክር ከሚገኝበት ቦታ (Beratungsstelle)፣ ወይም ደግሞ የስደተኞች ምክር ቤት (Flüchtlingsrat)) ምክር ማግኘት ትችላላችሁ። ጉዳዩን ፍርድቤት(Gericht) ማቅረብና በውጤቱ እንደማትስማሙ መናገር ትችላላችሁ። አንድ ከተማ ውስጥ ዕድሜያችሁ ከ18 ዓመት በታች መሆኑ ተቀባይነት ካላገኘና ሌላ ቦታ ከተመደባችሁ እዚያ ለሚገኘው የወጣቶች ተቋም ከ18 ዓመት በታች መሆናችሁ መናገር ትችላላችሁ። አንዳንድ ጊዜ ሌላ የወጣቶች ተቋም ሊያምኗችሁና ከቀድሞ በተለየ መልክ ሊወስን ይችላል።

17? 18? 14?

ሞግዚቶቻችን ለእኛ ምን ያደርጉልናል?

ዕድሜያችሁ 18 ዓመት እስካልሞላ ድረስ በጥሩ ሁኔታ መሆናችሁን የሚከታተልና ለእናንተ ኃላፊነት የሚወስድ ሰው መኖር አለበት። 18 ዓመት ካልሞላችሁ መፈረም ኣይፈቀድላችሁም ብዙ ነገርም ብቻችሁን አትችሉም። ስለዚህ ለመወሰን የሚረዳችሁ እና እንደናንተ ሆኖ የሚፈርምላችሁ ሰው ይመደብላችኋል።

ሞግዚታችሁ ለእናንተ ከመቆም ኣልፈው ምን እንደምትፈልጉ ይጠይቋችኋ።

ሞግዚታችሁ የእናንተን መብት መጠበቁን ጥብቅ ክትትል ያደርጋሉ። ለምሳሌ በትምህርት ቤት፣ በሞያ ስልጠና/ትምህር፣ ጥሩ የሆነ የመኖሪያ ቦታና በሌላም ብዙ ነሮች።
ከዚህ በታች አንዳንድ ምሳሌዎች ሰፍረዋል፤

- የጥገኝነት ማመልከቻ (Asylantrag) ለማስገባት ከፈለጋችሁ ሞግዚቶቻችሁ ማመልከቻውን ማስገባትና ስለ በጥገኝነት ሂደቱ ዘሚደረገው ቃለ-መጠይቅ (Interview im Asylverfahren) ያለማምዷችኋል።
- የሰውነት ማጠንከሪያ ቦታ“McFit“ ውል ለማድረግ ከፈለጋችሁ ሞግዚቶቻችሁ መፈረም አለባቸው።
- የቀዶ-ጥገና የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ በመጀመሪያ ሞግዚቶቻችሁ ማወቅና የቀዶ-ጥገናው አስፈላጊ መሆኑና አለመሆኑን ይወስናሉ።
- ሞግዚቶቻችሁ ትምህርትቤት መፈለግ አለባቸው፤ ወይም ደግሞ ትምህርትቤት መቀየር ከፈለጋችሁ ለሞግዚቶቻችሁ መናገር አለባችሁ።
- ከተማሪዎች ጋር በትምህርትቤት በኩል ወደ ጉዞ ለመሄድ የምትፈልጉ ከሆነ ሞግዚቶቻችሁ መወሰንና መፈረም አለባቸው።
- ፖሊስ ጋር ችግር ካጋጠማችሁና ፍርድቤት መቅረብ ካለባችሁ ሞግዚቶቻችሁ ማወቅና መወከል አለባቸው።
- ሞግዚቶቻችሁ የት እንደምትኖሩና፣ አንድ ሌሊት ሌላ ከተማ ሄዳችሁ ጓደኞቻችሁን መጎብኘት የምትችሉ እንደሆነ ይወስናሉ።

መቼ ነው ሞግዚት የምናገኘው?

ከ18 ዓመት በታች ከሆናችሁና፣ ያለ ወላጆቻችሁ ብቻችሁን ጀርመን አገር ከመጣችሁ ሞግዚት ይመደብላችኋል። ከጥቂት
ሳምንታት በኋላ አንድ የሴት ወይም የወንድ ሞግዚት ይመደብላችኋል። አልፎ አልፎ ጥቂት ወራትም ሊፈጅ ይችላል።
ሞግዚቶቻችሁን እስክትተዋወቋቸው ድረስ ጥቂት ጊዜያት ልፈጅ ይችላል ሞግዚቶች
ካልተመደቡላችሁ ኃላፊነቱን የሚወስደው የወጣቶች ተቋም ነው። ቤተሰባችሁን ወይም ዘመዶቻችሁ እንደሞግዚት ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉበት ሁኔታም አለ። ነገር ግን እነሱ ስለ ጥገኝነት ማመልከቻና ክንውን፣ ስለ ወጣቶች ዕርዳታ(Jugendhilfe) ፣ ስለ ጀርመን አገር ህግና ስለሌሎች ነገሮችም ጥሩ ዕውቀት ሊኖኖራቸው ይገባል። ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ችግር ካለባችሁ ከወጣቶች ተቋም ድጋፍ እንዲሰጣችሁና ሞግዚ እንዲመደቡላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ።
በመሰረቱ ጀርመን አገር 18 ዓመት እስኪሞላችሁ ድረስ ሞግዚቶች ይኖራችኋል። ከሌላ አገር ከመጣችሁና አቅመአዳም/አቅመሄዋን (Volljährig) የምትደርሱት በ20 ዓመት ወይም ከዚያ አልፎ ከሆነ፣ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ጀርመን አገር ሞግዚቶች ይመደቡላችኋል።

ልዩ ልዩ የሆኑ የሞግዚትነት ዐይነቶች አሉ፤ ከሚታወቁት ውስጥ፣

1. በመንግስት ተቋም ስር ያለ ሞግዚትነት
   እነዚህ ሞግዚቶች መንግስታዊ በሆነ የወጣቶች ተቋም ተቀጥረው የሚሰሩ ናቸው። እነሱ ብዙ ወጣቶችን ስለሚንከባከቡ፣ ለእያንዳንዱ ወጣት የሚሆን ጊዜ ያጥራቸዋል

2. ሳይከፈላቸው በፍቃዳቸው እንደሞግዚትነት የሚሰሩ፤ የክብር ሞግዚትነት
   ፈቃደኛ የሆኑት ሞግዚቶች ብዙ ጊዜ ያላቸው ናቸው። አብዛኞቹ የክብር ሞግዚቶች ከወጣቶች ጋር የሚገናኙት ቅዳሜ እና እሁድ ሲሆን፣ አብረው ጥሩ ግዜ ያሳልፋሉ

በሞግዚቶቻችሁ ደስተኛ ካልሆናችሁና፣ ችግር ካለባችሁ ወይም ደግሞ ጥሩ ግኑኝነት ከሌላችሁ ስለዚህ ጉዳይ ከሚንከባከቧችሁ ጋር ወይም ከወጣቶች ተቋም ጋር መነጋገር ትችላላችሁ። ምናልባት እናንተን በደንብ የሚይዙ ሞግዚቶች ልታገኙ ትችሉ ይሆናል።

ተንከባካቢዎቻችን ለእኛ ምን ያደርጉልናል ?

በመጀመሪያው ወቅት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች (unbegleiteten minderjährigen Flüchtlingen) ከሆኑ ልጆች ጋር አንድ ቤት ውስጥ፣ ተለቅ ያለ ቤት ውስጥ ወይም ሆስቴል አብራችህ ትኖሩ ይሆናል። እዚያ እያንዳንዱ ወጣት ልጅ አንድ የወንድ ወይም የሴት ተንከባካቢ አለው። እነሱም እናንተን እለታዊ ኑሮአችሁ፣ ለምሳሌ ሃኪም ጋር ቀጠሮ ካላችሁ፣ ወደ ገበያ የምትሄዱ ከሆነና፣ የትምህርትቤት ስራም እንዲያግዟችሁ ከፈለጋችሁ ይረዷችኋል። ማን እንደሚንከባከባችሁ ራሳችሁ መወሰን አትችሉም። ከሚንከባከቧችሁ ሰዎች ጋር ችግር ካለባችሁ ግን ከሞግዚቶቻችሁ ወይም ከወጣት ተቋሙ ጋርመነጋገር ትችላላችሁ። ምናልባት አዲስ የሚንከባከቧችሁ ሰዎች ሊመደቡላችሁ ይችላሉ።

የት ነው የምንኖረው ?

ከሁለት እስከ አራት ወሮች ባሉት ጊዚያት ውስጥ ቋንቋውን ትንሽ ከተማራችሁና ከአገሩ ሁኔታ ጋር ከተለማመዳችሁ በኋላ፣
የወጣቶች ተቋም ከአናንተና ከሞግዚቶቻችሁ ጋር በመሆን የት መኖር እንደምትችሉ ይወስናሉ።
የተለያዩ አማራጮችም አሉ፤ እስካሁን እንደኖራችሁት ከሌሎች ወጣቶችና ከተንከባካቢዎቻችሁ ጋር ለመኖር ከፈለጋችሁ የወጣቶች መኖርያ ቦታ ወይም በግሩፕ ሆነው (Wohngruppe) የሚኖሩበት ቤት መኖር ትችላላችሁ። ለብቻችሁ ለመኖር የምትፈልጉ ከሆነ ለብቻ መኖሪያ ቤት ወይም ከሌላ ወጣቶች ጋር ተጋርታችሁ ለመኖር ትችሉ እንደሆነ መጠየቅ ትችላላችሁ። ሌላው አማራጭ ደግሞ ከቤተሰብ ጋር መኖር ነው። እነዚህም ዘመዶቻቹሁ ወይም ደግሞ ሌላ ቤተሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህም የሚንከባከቡ ወይም እንግዳን የሚያስተናግዱ ቤተሰቦች ተብለው በመጠራት ይታወቃሉ።
አይስማማችሁ ይሆናል? ሁኔታችሁን የሚከታተል የለም? ወይም ደግሞ የምታምኑት ሰው አጠገባችሁ የለም? በፈለጋችሁት ጊዜ ከወጣቶች ተቋም ጋር መነጋገር ትችላላችሁ። ሌላ ቦታ ለመኖር የምትፈልጉ ከሆነ ለወጣቶች ተቋም መናገር ትችላላችሁ። የወጣቶች ተቋምም ለአናንተ የሚስማማ ሌላ መኖሪያ ቦታ ማሳየት አለበት። ከትላልቅ ሰዎች ጋር መኖር የለባችሁም ።

ካመመን ምን ማድረግ እንችላለን ?

ጀርመን አገር በገባችሁ በመጀመሪያው ቀናት የሚተላለፍ በሽታ ይኖርባችሁ እንደሆን ለማወቅ ምርምራ ይደረግላችኋል። በሽታ ካለባችሁ ህክምና ይደረግላችኋል።
ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አንድ ቦታ ላይ የሰውነትም ሆነ የመንፈስ ችግር ካለባችሁ ምን ማድረግ ትችላለችሁ?
ሃኪም ጋር በመሄድ ስላለባችሁ ችግር የመናገርና የመታከም መብት አላችሁ።

- ፍርሃት አለባችሁ?
- የሚያስጨንቅ ሃሳብ አለባችሁ?
- የራስ ምታት አለባችሁ?
- በጣም ይደክማችኋል?
- የእንቅልፍ ችግር አለባችሁ?
- ትኩሳት አለባችሁ?
- የጥርስ ህመም አለባችሁ?
- የተሰበረ እግር አላችሁ?

ከሚንከባከቧችሁ፣ ከሞግዚቶቻችሁ ወይም ከወጣቶች ተቋም ጋር ተነጋገሩ። የሃኪም ቀጠሮ ለመያዝ ይረዷችኋል።
የጀርመን ቋንቋ በደንብ የማትናገሩ ከሆነ አስተርጓሚ ይዞ የመሄድ መብት አላችሁ።
ወጪውን ማነው የሚከፍለው?
አብዛኛውን የህክምና ዕርዳታ መንግስት ነው የሚከፍለው። በአንድ አንድ ከተማዎች የጤንነት ካርድ ይሰጣል፤ በአንዳንድ ከተማዎች ደግሞ ተጨማሪ ወረቀት በወጣቶች ተቋም በኩል ይሰጣል። ለመመርመር ከፈለጋችሁና ፈቃድ ማግኘት የማትችሉ ከሆነ በሞግዚቶቻችሁ በኩል በወጣቶች ተቋም ማስፈጸም አለባችሁ።



ተጨማሪ መረጃዎች ለወጣት ሴቶች፤

ጀርመን አገር ወጣትና ትላልቅ ሴቶች ቢያንስበዓመት አንድ ጊዜ የሴት ሃኪም (Frauenarzt) ጋር ይሄዳሉ። ሁሉም ነገር ደህና መሆኑን ለማወቅ ምርመራ (Vorsorgeuntersuchungen) ይደረጋል። ሴቶች በሚያረግዙበትም ጊዜም ሃኪሞቹ ምርምራ ለማድረግ ዝግጁ ናቸው። እርግዝናን ለመከላከል የሚጥቅሙ መረጃዎችም ይሰጣሉ። መጥፎ ነገር ካጋጠማችሁም ይመረምሯችኋል።

Out of Action
im Monat

ይህንን መጽሄት አንድ ላይ ሆነን ያዘጋጀነው እኛ የወጣቶች ግሩፕ ነን። እድሜያችን ከ16 እስከ 30 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የሚገኝ ሆኖ በርሊን፣ ብራንደንቡርግና ኖርድ ራይን ቬስትፋለን ነው የምንኖረው። ስለእኛ የበለጠ መረጃ በዚህ መጽሄት የመጨረሻው ገጽ ላይ ማግኘት ትችላላችሁ።

ሃቫ ስለ ግሩፑ ፤

„ከእናንተ ጋር ጥሩ ጊዜ ነበር። ከእኛ ውስጥ ኣንድ ኣንዶቹ ገና ጥሩ ጀርመንኛ አይናገሩም ነበር፤ ይሁንና ሁላችንም አንድ ዓይነት ዓላማ ነበረን፡ ለመገናኘት፥ ምክንያቱም ስንገናኝ ብዙ እንሆናለን። ከስራ ገለፃ (Workshops) በኋላ አብረን በልተን ትልቅ ደስታም ነበረን። የምንፈልገው እዚህ ጥሩ ጊዜ ማሳለፍና ሌሎችንም መርዳት ነበር። ምክያቱም እኛም ችግር ነበረብን። አንዱ ሌላውን ይረዳል። የስራ ገለፃው ተጠናቋል፤ ነገር ግን አሁንም ቢሆን ግኑኝነት ኣለን። ከእናንተ ጋር ያሳለፍነው ጥሩ ጊዜ በቃላት ሊገለጽ የሚችል ነገር አይደለም። ልክ እንደ አንድ ቤተሰብ ነበርን።“

መኖር

ጀርመን አገር መኖር ይፈቀድልኛል ወይ?

የሚያሳዝነው ነገር አብዛኛው የዓለም ህዝብ ለመኖር የሚፈልገውን አገር መምረጥ አይችልም። ጀርመን ለመኖር ከፈለጋችሁ፣ ወይም ደግሞ ሌላ የአውሮፓ አገር ለመሄድና እዚያ ለመኖር ካሰባችሁ ፈቃድ ያስፈልጋችኋል። የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘት ትችሉ እንደሆን የሚወስነው የመንግስት ተቋም ነው። ዕድሜያችሁ ከ18 ዓመት በታች ከሆነና ጀርመን ኣገር ብቻቹ ከሆናቹ ሁለት አማራጮች አሉ።

1. የመጠጊያ/የጥገኝት ማመልከቻ (Asylantrag) ማስገባት ትችላላችሁ።
2. ጥገኝነት ሳትጠይቁ የመኖሪያ ፈቃድ (Aufenthalt) እንዲሰጣችሁ ማመልከት ትችላላችሁ።

አስፈላጊ፤ ጀርመን አገር ለመቆየት እንድትችሉ ሞግዚታቹ ማመልከቻ ያስገባል። ሞግዚት ከሌላችሁ የወጣቶች ተቋም ማመልከቻውን ሊያስገባ ይችላል።

የትኞቹ የመንግስት መስሪያቤቶች ናቸው አስፈላጊዎች?

,,„Das BAMF“

ፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ቢሮ

ፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ቢሮ (BAMF) መንግስታዊ ተቋም ነው። የመጠጊያ ማመልከቻ ጀርመን አገር ካስገባችሁ የዚህ ተቋም (BAMF) ሰራተኛ ቃለ- መጠይቅ ያደርግላችኋል። ፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ቢሮ ምን አይነት የጥገኝነት ፈቃድ (Asyl, Flüchtlingsstatus ወይም subsidiären Schutz) እንደሚሰጥህ ይወስናል።

ከዚህ በተጨማሪ ይህ የመንግስት ተቋም ከመጣችሁበት አገር በእርግጥ ለህይወታችሁ የምያሰጋ ነገር ካለና ጀርመን ኣገር መቆየት እንደምትችሉ ያጣራል።

ይህ የመንግስት ተቋምም (BAMF) ውሳኔውን ለእናንተም ሆነ ለኢሚግሬሽን ቢሮ (Ausländerbehörde) ያሳውቃል።

„Die Ausländerbehörde“

የኢሚግሬሽን ቢሮ

የኢሚግሬሽን ቢሮ በየትኛውም የጀርመን ከተማና ወረዳ ይገኛል።

የጥገኝነት ማመልከቻ ካላስገባችሁ ወደ ኢሚግሬሽን ቢሮ (Duldung) ክዚህ ኣገር ሳትባረሩ እንድትቆዩ የሚሰጥ ግዝያዊ የመኖርያ ፈቃድ ወይም ሌላ ዐይነት የመኖሪያ ፈቃድ (Aufenthaltstitel) እንዲሰጣችሁ ማመልከቻ ታስገባላችሁ። በፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ቢሮ (BAMF) የጥገኝነት ማመልከቻ

ካስገባችሁ የኢሚግሬሽን ቢሮ ለግዜው ለመኖር የሚያስችል Aufenthalts-gestattung የተባለ የመኖርያ ፈቃድ ይሰጣችኋል። የኢመግረሽን ቢሮ የጥገኝነት ማመልከቻችሁ ውሳኔ ላይ መድረሱ ከ BAMF ሲነገረው ሌላ ስም ያለው የመኖርያ ፈቃድ ይሰጣችኋል።

የኢሚግሬሽን ቢሮ በመኖርያ ፈቃዱ ላይ የስራ ፈቃድና ወደ ሌላ የጀርመን ከተማ መዘዋወር የምትችሉ መሆኑን (Residenzpflicht) ማህተም ያደርግላችኋል።

የኢሚግሬሽን ቢሮ ቀጠሮ በጣም አስፈላጊና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የሚያስቸግር ነው። ከምታምኑት ሰው ጋር አብራችሁ የመሄድ መብት አላችሁ።

አማራጭ 1፤ የጥገኝነት ማመልከቻ ማስገባት መብት አላችሁ!

ስደተኛ ማለት ከአገሩ ወጥቶ ሌላ አገር መጠለያ/መጠግያ የሚፈልግ ማለት ነው። ጀርመን አገር ልዩ ልዩ ለስደተኞች መጠለያ „Flüchtlingsschutz“ መስጠት የሚቻልበት የተለያየ የህግ ዐይነት አለ። የጥገኝነት ማመልከቻ ካስገባችሁ „Asyl“, „Flüchtlingsschutz“, „Subsidiären Schutz“ oder „Abschiebeverbot“ የመሳሰሉትን ለመቆየት የሚያስችሉ የመኖርያ ፈቃድ ዐይነቶች ማግኘት ይቻላል።



Abschiebeverbot = በግድ ማስወጣትን/ማባረርን መከልከል

Abschiebehindernis = በግድ ማስወጣትን/ማባረርን ማሰናከል

አልፎ አልፎ የፓስፖርት ምትክ

+

የመኖሪያ ፈቃድ



Duldung መባረር ወይም በግድ ማስወጣቱ ቀርቶ ለጊዜው የሚሰጥ ይመኖርያ ፈቃድ

“Asyl bekommen“፣ „Flüchtlingsschutz bekommen“ „Subsidiären Schutz bekommen“ ማለት ጀርመን አገር በሚቀጠሉት ጊዜያት እንድትቆዩ ፈቃድ ይሰጣችኋል ማለት ነው። ከዚያ በኋላ ሁልጊዜ እዚህ መቆየት የምትችሉ እንደሆን ይወሰናል። በመጀመሪያ ጊዜ ለአንድ ወይም ለሶስት ዐመት የመኖሪያ ፈቃድ ይሰጣችኋል።

„Abschiebeverbot“ በግድ ማስወጣትን/ማባረርን መከልከል ማለት ለጊዜው አገራችሁ ብትመለሱ አደጋ ላይ ትወድቃላችሁ፣ ለምሳሌ ዕድሜያችሁ ከ18 ዐመት በታች በመሆኑ ወይንም ደግሞ በሽታ ይዞአችሁ ከሆነ እዚያ መታከም ስለማይቻል ነው። ስልሆነም ለመጀመሪያ ጊዜ ለአንድ ዐመት የሚሆን የመኖሪያ ፈቃድ ይሰጣችኋል፤ በኋላ ደግሞ ረጅም ጊዜ ለመኖር ትችሉ እንደሆን ታይቶ ይወሰናል። ስለዚህ ጉዳይ ተጨማሪ መረጃ በአማራጭ ሁለት „Möglichkeit 2“ ላይ ማግኘት ይቻላል።

„Abschiebehindernis„ በግድ ማስወጣትን/ማባረርን ማሰናከል ማለት አስፈላጊው የመውጫ ወረቀቶች (Reisedokumente) ስለሌሏችሁ ወደ አገራችሁ መመለስ አይቻልም ማለት ነው። ወይንም ደግሞ በጣም ከታመማችሁ በአውሮፕላን ለመጓዝ የማትችሉ ከሆነ እናንተን በግድ ማስወጣት/ማባረር አይቻልም ማለት ነው። ማባረርን ማሰናከል (Abschiebehindernis) የሚለው ምክንያት ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ከሆነ Duldung (መባረር ወይም በግድ ማስወጣቱ ቀርቶ ለጊዜው የሚሰጥ የመኖርያ ፈቃድ) ይሰጣችኋል። ስለዚህ ጉዳይ ተጨማሪ መረጃ በአማራጭ ሁለት „Möglichkeit 2“ ማግኘት ይቻላል።

ጥገኝነት ላመልክት ወይ?

ጀርመን አገር ጥገኝነት ለማመልከት ከፈለጋችሁ ረዘም ላለ ጊዜ አስቡበት። ከሞግዚቶቻችሁ፣ ከተንከባካቢዎቻችሁና ከወጣቶች ተቋም ጋር በመሆን የጥገኝነት ማመልከቻ ለማስገባት ፍላጎት ይኖራችሁ እንደሆን በደንብ ተነጋገሩ። በመጀመሪያ በቂ ምክር ካገኛችሁ ስለማመልከቻው በደንብ ከተረዳችሁና፣ እንዲሁም ደግሞ በሂደቱ የምትስማሙ ከሆነ ጥገኝነት አመልክቱ። የግዴታ መጠለያነት ማመልከት የለባችሁም፤ ይህ የእናንተ ነጻ ምርጫ ነው። የመጠለያነት ማመልከቻው ከገባ በኋላ ረጅም ጊዜ ይፈጃል። ስለሆነም አንድ ጊዜ ከጀመራችሁ በኋላ እስከመጨረሻው ድረስ በነገሩ መግፋት ይኖርባችኋል።
ጀርመን አገር ጥገኝነት ለማግኘት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ከዚህ በታች አንዳንድ ምሳሌዎች ብቻ ሰፍረዋል፤

- ካለፈቃዳችሁ እንድታገቡ ከተገደዳችሁ (Zwangsheirat)
- ወታደር እንድትሆኑ ወይም ደግሞ ለአንድ ወታደር ተቋም እንድትሰሩና እንድትዋጉ ከተገደዳችሁ (Kindersoldat)
- ዕፅ ለማመላለስና ለመሸጥ ወይንም ደግሞ የሴተኛ አዳሪ እንድትሁኑ ከተገደዳችሁ (Menschenhandel)
- ለሴት ልጆች፤ መገረዝ ካለባችሁ(Genitalverstümmelung)

ምን ማድረግ አለብኝ?

የስደተኝነት/ የመጠለያነት ማመልከቻ ካስገባችሁ በአንድ የፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ቢሮ (BAMF) ሰራተኛ ቃለ-መጠይቅ ይደረግላችኋል። ለቃለመጥይቁ መዘጋጀት ይኖርባችኋል። ከየት አገር እንደመጣችሁና፣ እንዴትስ እንደመጣችሁ ጥያቄ ይቀርብላችኋል። በተጨማሪም ለምን መጠለያነት/ጥገኝነት እንዳመለከታችሁና ምክንያቱ ምን እንደሆነ፣ ለዚህ ደግሞ ማረጋገጫ ወረቀቶች ከአገራችሁ ይዛችሁ መመጥታችሁ፣ የሌላችሁ ከሆነ ደግሞ ማስመጣት ይቻል እንደሆን ትጠየቃላችሁ።
ሞግዚቶቻችሁን ወይም የሚንከባከቧችሁን ስለጥገኝነቱ ሂደት ገለጻ እንዲሰጧችሁ የመጠየቅ መብት አላችሁ። እነሱ ለእናንተ ብዙ ነገሮችን ይፈጽማሉ፤ ዕርዳታም የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ ይረዷችኋል። ሞግዚቶቻችሁ በቃለ-መጠይቁ ጊዜ አብረዋችሁ እንዲሆኑ መብት አላችሁ። በተጨማሪም አስፈላጊ በሆኑ ቀጠሮዎች ላይ የሚተረጉምላችሁ ሰው እንዲቀመጡላችሁ መብት አላችሁ። በፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ቢሮ ሁልጊዜ የራስችሁን ቋንቋ የሚናገር ሰው ይኖራል። ትርጉሙ ካልገባችሁ ሌላ የሚተረጉምላችሁ ሰው እንዲመጣ የመጠየቅ መብት አላችሁ።

ሴት ልጆች ከሆናችሁ ሴት ጠያቂና ኣስተርጓሚ ከፈለጋችሁ ቀደም ብላችሁ የቃለ-መጠይቁ ቦታ መናገር ትችላላችሁ። እንዲዚሁም ወንድ ወጣት ልጆች ከሆናችሁ ወንድ ጠያቂና ኣስተርጓሚ እንዲመደብላችሁ የመናገር መብት አላችሁ። የቃለ-መጠይቁ ቦታ በደንብ የሚያዳምጣቹና የሚረዳቹ አንድ ሰው ይዛችሁ የመምጣት መብት አላችሁ። የሚሻለው ቃለ-መጠይቁን እንድትዘጋጁ የረዳችሁን ሰው ይዞ መሄዱ ነው።

ዕድሜያችሁ 14 ዓመት ካልሞላ በእናንተ ፈንታ ሞግዚቶቻችሁ እንዲሄዱላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ። ሞግዚቶቻችሁ የነገራችኋቸውን በሙሉ መጻፍ አለባቸው። ከዛ በኋላ እናነተ ቃለ-መጠይቁ ላይ መገኘት አያስፈልጋችሁ እንደሆነ ፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ቢሮ (BAMF) ይወስናል።

ከቃለ-መጠይቁ በኋላ የተናገራችሁት መዝገብ (Protokoll) በሙሉ ተጽፎ ይላክላችኋል። የተመዘገበው/የተጻፈው መልሳችሁ አስኪላክላችሁ ድረስ በጣም ረጅም ጊዜ ሊፈጅ ይችላል። የተናገራችኋቸው በሙሉ በትክክል ተተርጉመውና ተጽፈው እንድሆነ ከኣስተርጓሚ ጋር በመሆን በደንብ ማየት አለባችሁ። የማትስማሙ ከሆነ መጨመር፣ ማረምና እንዲሁም ይህንን ለሚመለከተው ተቋም መላክ ትችላላችሁ።

ከዚያ በኋላ ውሳኔው እስኪመጣ ድረስ መጠበቅ አለባችሁ። በውሳኔው ላይ መጠለያ/ጥገኝነ፣ የስደተኝነት መከላከያ፣ የዕርዳታ መከላከያ ወይም ደግሞ እንዳትባረሩ የሚያግድ „Abschie-beverbot“ ተብሎ ይሰፍርበታል፤ ወይም እነዚህን ነገሮች ማግኘት እንደማትችሉ ይጻፍበታል። ውሳኔው ብዙ ሳምንታትና ወራት ሊፈጅ ይችላል። ውሳኔው አዎንታዊ ከሆነ ወይም ማምልክቻው ተቀባይነት ካገኘ የመኖሪያ ፈቃድ ይሰጣችኋል። ውሳኔው ተቀባይነት ካላገኘ ቶሎ ብላችሁ ከሞግዚቶቻችሁ፣ ወይም ደግሞ ከተንከባካቢዎቻችሁ ጋር በመሆን ጠበቃ ጋር ግኑኝነት ማድረግ። ከጠበቃ ጋር በመሆን አሉታዊ ውሳኔውን ይዛችሁ ፍርድቤት መክሰስ ትችላላችሁ።

„Aufenthaltsgestattung" ለመኖር መፍቀድ ማለት ምን ማለት ነው?

Aufenthaltsgestattung ማለት የጥገኝነት ማመልከቻ ካስገባችሁ ጀምሮ የሚሰጥ የመኖሪያ ፈቃድ ነው። ይህ የመኖሪያ ፈቃድ በኢሚግሬሽን ቢሮ በኩል የሚሰጥ ነው።

Sichere Herkunftsstaaten ስጋት የሌለባቸው አገሮች ማለት ምን ማለት ነው?

ጀርመን አንዳንድ አገሮችን ስጋት የሌለባቸው አገሮች (sicheren Herkunftsstaaten) ናቸው ብላ ወስናለች። ጀርመን ኣገር ከእነዚህ አገሮች የሚመጡ ሰዎች ጥገኝነት ለመጠየቅ የሚያስችል በቂ ምክንያት እንደሌላቸው ነው የምታምነው። የጀርመን መንግስት ከእነዚህ አገሮች የሚመጡ ሰዎች ወደ አገራቸው መመለስ እንደሚችሉ፤ ምንም የሚያሰጋቸው ነገር እንደሌለና ክትትል እንዳይደረግባቸውም የምያሰጋ ነገር የለም ይላል። ይህ የፖለቲካ ውሳኔ ሲሆን፣ እነዚህ አገሮች ውስጥ ሁሉም ሰዎች ያለስጋት ይኖራሉ ወይም ምንም አይደርስባቸውም ማለት ግን አይደለም። አብዛኛውን ጊዜ ከሌላው ዜጋ ለየት ባለ መንገድ በዝቅተኛነት ደረጃ የሚታዩ፣ ጭቆና የሚደርስባቸውና ክትትልም የሚደረግባቸው ይኖራሉ።

አስፈላጊ፤ ስጋት የለበትም ከሚባል አገር ከመጣችሁ ጥገኝነት ለመጠየቅ የራሳችሁ የሆነ በቂ ምክንያት ሊኖ ራችሁ ይችላል። አገራችሁ ስጋት የለባቸውም ከሚባሉ አገሮች ውስጥ ትመደብ እንደሆነ ለሞግዚቶቻችሁ ወይም ለሚንከባከቧችሁ መናገርና፣ ስደተኞችን ስለጥገኝነት ሂደት የሚያማክር ቢሮ በመሄድ ምክር ማግኘት አስፈላጊ ነው።



አማራጭ 2፣

ጥገኝነት ሳታመለከቱ የሚኖሯችሁ መብቶች!

ጀርመን አገር ከሆናችሁ ዕድሜያችሁ 18 ዓመት እስኪሞላው ድረስ የወጣቶች ተቋማት ይንከባከባችኋል። እዚህ ላይ ምንም ዐይነት ማመልከቻ ብታስገቡም ባታስገቡም የምያመጣው ለውጥ የለም። ከ18 ዓመት በታች ከሆናችሁ እንዲሁም ብቻችሁን ከመጣችሁ ማባረርን የሚከለክል ግዝያዊ የመኖርያ ፈቃድ ይሰጣችኋል። 18 ዓመት ስላልሞላችሁና ብቻችሁን ስለመጣችሁ፡ የወጣቶች ተቋማት እናንተን መንከባከብ አለባቸው፣ እናንተን አስገዶ ወደ አገራችሁ ማስወጣትም አይፈቀድም።

አስፈላጊ፣ ወላጆቻችሁ፣ በአገራችሁ እናንተን የማሳደግ መብት ያለው ሰው ወይም ደግሞ ልጆችን መጠጊያ የሚሰጥ ድርጅት እናንተን ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን ለጀርመን ኢምግሬሽን ቢሮ በጽሁፍ ማረጋገጫ ከላኩ „አስገድዶ ማስወጣትን ማሰናከል የሚለው ዕድሚያቸው 18 ዓመት ላልሞላ የምያገለግል ህግ" ለእናንተ አይሰራም።
ወደ ትውልድ አገራችሁ መመለስ የማትችሉ ከሆነና ጥገኝነት የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ ከሞግዚቶቻችሁ ወይም ከሚንከባከቧችሁ ጋር ጥገኝነት ማመልከት ይኖርባችሁ እንደሆን መመካከር አለባችሁ።

„Aufenthalt aus humanitären Gründen" የመኖሪያ ፈቃድ በሰብአዊነት ምክንያት ማለት ምን ማለት ነው?
የጥገኝነት ማመልከቻ በማስገባት ፈንታ የሰብአዊነት ምክንያትን በማድረግ Aufenthalt aus humanitären Gründen የሚባል የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት ይቻላል። ይህንን የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ሰብአዊ ምክንያቶች ማቅረብ ይኖርባችኋል። ለምሳሌ ቤተሰቦቻችሁ በህይወት እንደማይኖሩ፣ ብትመለሱ አደጋ ሊደርስባችሁ እንደሚችል፣ በሽታ ካለባችሁ እዚያ በቂ ህክምና ማግኘት እንደማይቻልና ሌላም ምክንያቶች መስጠት ይቻላል። ማመልከቻውን ሞግዚቶቻችሁ ወይም ደግሞ የወጣቶች ተቋም ለኢሚግሬሽን ቢሮ ሊያስገብላችሁ ይችላሉ። ለማንኛውም ቀደም ብላችሁ ከሞግዚቶቻችሁ ወይም ከተንከባካቢዎቻችሁ ጋር መነጋገር ያስፈልጋል።
Duldung („Aussetzung der Abschiebung") አስገድዶ ማስወጣትን የሚከለክል/የምያስቀር ግዝያዊ የመኖርያ ፈቃድ ማለት ምን ማለት ነው?
18 ዓመት እስኪሞላችሁ ድረስ ሞግዚቶቻችሁ፣ ወይም ደግሞ የወጣቶች ተቋም አስገድዶ ማስወጣትን የሚከለል/የምያስቀር የመኖርያ ፈቃድ (Duldung) እንዲሰጣችሁ የኢሚግሬሽን ቢሮ ጋር ማመልከቻ ሊያስገቡላችሁ ይችላሉ። ይህንን የመኖርያ ፈቃድ ልታገኙ የምትችሉት ዕድሜያችሁ 18 ዐመት ካልሞላ፣ ትምህርትቤት ከሆናችሁ ወይም ደግሞ የሙያ ስልጠና የምትማሩ ከሆነ ነው። አስገድዶ ማስወጣትን የሚከለል/የምያስቀር የመኖርያ ፈቃድ ቀጥሎ የሚገኙት ምክንያቶች እስኪቀሩ ድረስ ሊራዘም ይችላል። እነሱም፣ ትምህርት ወይም የክሙያ የሞያ ስልጠና እስኪጠናቀቅ ድረስ፣ ዕድሜያችሁ 18 ዐመት እስኪሞላ ወይም እዚህ አገር ብዙ ዓመታት ከቆያችሁና እንዲሁም የስራ ቦታ ካገኛችሁና „Aufenthaltserlaubnis" የሚባል የመኖሪያ ፈቃድ የማግኘት መብት ካገኛችሁ ነው።

„Ausbildungsduldung“ የሞያ ስልጠና ለማድረግ የሚሰጥ ጊዜያዊ ፈቃድ ማለት ምን ማለት ነው?

አንድ ኩባንያ ውስጥ የሙያ ስልጠና ዕድል ካገኛሁ ሞግዚቶቻችሁ የሞያ ስልጠናው እስኪጠናቀቅ ድረስ ከጀርመን አገር እንዳትባረሩ የሚከላከል የመኖርያ ፈቃድ (Duldung) እንዲሰጣችሁ ወደ ኢሚግሬሽን ቢሮ ማመልከቻ ሊያስገቡላችሁ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ይህ ዐይነቱ ጊዚያዊ የመቆያ ፈቃድ ትምህርት ቤት ገብተው መማር ለሚፈልጉም ሊያገለግል ይችላል። ስለዚህ ፈቃድ ከሞግዚቶቻችሁ ጋር በመሆን አማካሪ ቢሮ ወይም ኢሚግሬሽን ቢሮ በመሄድ መጠየቅ ያስፈልጋል። የኢሚግሬሽን ቢሮ ስጋት የለባቸውም ከሚባሉ አገሮች („sicheren Herkunftsländer“) ለሚመጡ ሰዎች እና በሌላ ምክንያት ግደባ ስለሚያደርግ የስራ ፈቃድ አይሰጥም(Sanktionen)። ስለ መብታችሁ እና ስላላችሁ አማራጭ ከሞግዚቶቻችሁ ወይም ደግሞ ከሚንከባከቧችሁ ጋር መነጋገር ያስፈልጋል።

ለምንድን ነው የማይፈቀድልኝ/እገዳ የሚደረግብኝ?

አልፎ አልፎ የኢሚግሬሽን ቢሮ መሟላት ያለባቸው ነገሮች ይጠይቃሉ። ለምሳሌ ፓስፖርት (Pass) እንድታቀርቡ ይጠይቃችኋል። ይህንን የማታሟሉ ከሆነ የኢሚግሬሽን ቢሮ እገዳ „Sanktionen“ ያደርጋል፤ ለምሳሌ የስራ ፈቃድ ይከለከልና የሞያ ስልጠና ልታደርጉ ኣትችሉም።

የኢሚግሬሽን ቢሮ የሚፈልገው ነገር ካለ የግዴታ ከሞግዚቶቻችሁ ወይም ከሚንከባከቧችሁ ሰዎች ጋር መነጋገር አለባችሁ። የኢሚግሬሽን ቢሮ ማዕቀብ/እገዳ የሚያደርግባችሁ ከሆነ ሊረዷችሁና ሊያማክሯችሁ ይችላሉ።

ጀርመን ሳይቀበላችሁ ሲቀር፣ አገርን ለቃችሁ እንድትወጡ በሚነገራችሁ ጊዜና እንዲሁም በቀጥታ የምትባረሩ ከሆነ የሚኖር አማራጭ!

ከፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ቢሮ(BAMF) ወይም ከኢሚግሬሽን ቢሮ ማመልከቻችሁ ተቀባይነት ሳያገኝ ሲቀር፤ ወዲያውኑ የምትባረሩበት ውሳኔ ሳይሆን የመጀመሪያው አሉታዊ ውሳኔ ነው ማለት ነው። የመንግስት መስሪያቤቶችና ሰራተኞች ስህተት ስለሚሰሩ ውሳኔውን በመቃወም ፍርድቤት የመክሰስ (klagen) ዕድል አላችሁ። ውሳኔውን በመቃወም የመክሰስ ዕድል ያላችሁ ጊዜ በጣም አጭር ወይም በጥቂት ቀናት የሚቆጠር ነው። የመኖሪያ ፈቃድን በሚመለከት ምክር ሊሰጥ የሚችል ቦታና ጥሩ ጠበቃ ጋር በፍጥነት መሄድ ያስፈልጋል።

አስፈላጊ፤ የጥገኝነት ማመልከቻችሁ ከፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ቢሮ ተቀባይነት ካላገኘ(Ablehnung) ወይም ደግሞ የኢሚግሬሽን ቢሮ በሰብአዊነት ምክንያት የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘት አትችሉም የሚል ከሆነ ቶሎ ብላችሁ ከሞግዚቶቻችሁ ጋር መነጋገር ያስፈልጋል። በፈቃደኝነት አገር ለቃችሁ እንድትወጡ የተባላችሁ እንደሆነ ወይም ደግሞ የመባረር ፍርሃት ካለባችሁ ይህንንም ከእነሱ ጋር መነጋገር ያስፈልጋል። ምክር የሚሰጥበት ቦታና ጠበቃ በመፈላለግ ይረዷችኋል።

ማመልከቻው ተቀባይነት ካላገኘ ሌላ ተጨማሪ ዕድልም አለ፤ ለምሳሌ ማመልከቻው የሚታይበት መማፀኛ ቦታ „Petitionsverfahren“ ወይም የተለየ ሁኔታን የሚመረምር ቡድን „Härtefallkommission“፣ የቤተክርስቲያን መጠለያ „Kirchenasyl“ ሄዶ በመጠየቅና፣ ነገሩን ለጋዜጠኞችና ለሌላ የብዙሃን መገናኛ ሰዎች በማሳወቅ ማመልከቻው እንደገና እንዲታይ ማድረግ ይቻላል። የግዴታ የሚያማክር ሰው መፈለግና ስለሁኔታው ከሌላ ሰዎች ጋር መነጋገር በጣም ጠቃሚ ነው። በተቻለ መጠን በሚያስፈልጉ ነገሮች ላይ ሃሳባችሁን ሰብሰብ ማድረግ። ጉዳዩ አስጨናቂና አስቸጋሪ ነው፤ ነገር ግን በተቻለ መጠን ነገሩን ቀለል አድርጎ አለማየትና ከጓደኞቻችሁ፣ ከትምህርትቤት፣ ከሚንከባከቧችሁና ከሞግዚቶቻችሁ፣ እንዲሁም ደግሞ ከተለያዩ ደርጅቶች ጋር በመነጋገር መፍትሄ ሊገኝ ይችላል!

ቤተስቦቼን ጀርመን አገር ማስመጣት እችላለሁ ወይ?

18 ዓመት እስኪሞላችሁ ደረስ ጀርመን አገር ከቤተሰቦቻችሁ ጋር የመኖር መብት አላችሁ። ይህም ማለት ቤተሰቦቻችሁ ጀርመን አገር እስካልኖሩ ድረስ የመምጣት መብት አላቸው። ቤተሰቦቻችሁ ጀርመን አገር መምጣት የሚችሉ ከሆነ ዕድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላቸው ወንድሞቻችሁና፣ እህቶቻችሁ አብረው መምጣት ይችላሉ። ይህ ቤተሰብን በአንድ ላይ ማገናኘት „Familienzusammenführung“ ተብሎ ይጠራል። የሚያሳዝነው ነገር ቤተሰቦቻችሁ በቀላሉ ወደ ጀርመን አገር እንዳይመጡ የሚያከብድ ህግ አለ። የመክበዱ/የመወሳሰቡ ጉዳይ ሊወሰን የሚችለው እናንተ ባላችሁ የመኖሪያ ፈቃድና በዕድሜያችሁ መሰረት ነው።

ምን ምን ነገሮች መሟላት አለባቸው ?

በመጀመርያው ደረጃ ጥገኝነት ወይም የስደተኛነት ድጋፍ (Flüchtlingsschutz) ማግኘታችሁ ነው። የዕርዳታን ድጋፍ በሚመለከት ለየት ባለ መልክ እንዲታይ መሞከር። ለየት ያለ ህግ ስለሚኖር ባላችሁ የመኖሪያ ፈቃድ ማስመጣት ይቻል እንደሆን መጠየቅ ወይም መረጃ ማግኘት አስፈላጊ ነው።

በሁለተኛው ደረጃ ጥገኝነት ስትጠይቁና ወላጆቻችሁ ጀርመን ኣገር ሲገቡ ዕድሚያችሁ ከ18 ዓመት በታች ከሆነና ኣባታችሁ ይሁን እናታችሁ እዚህ የማይኖሩ ከሆነ ነው።

እነዚህ ሁኔታዎች ከተሟሉ ቤተሰቦቻችሁ ከእህቶቻችሁና ከወንድሞቻችሁ ጋር በመሆን የጀርመን ኤምባሲ ጋር ሄደው እናንተ ጋር ለመቀላቀል እንደሚፈልጉ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ማመልከቻውን ማስገባት ያለባቸው በሚኖሩበት አገር ነው። በዚህ ኣሰራርም ለየት ያለ ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

ሂደቱ የተወሳሰበ ነው። ጠበቃችሁ ወይም ይህንን ጉዳይ የሚመለከትና የሚያማክር ቦታ የተሻለ መረጃ ሊሰጧችሁ ይችላሉ። እነሱ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ይነግሯችኋል። ሌላው አማራጭ፣ ቤተሰቦቻችሁ በአውሮፓው አንድነት(EU) አንድ አገር ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ እዚያ ሄዶ የጥገኝነት ሂደቱን መቀጠል ይቻላል። ይህ ጉዳይ በጀርመን በኩል የሚቀነባበር ወይም የሚካሄድ ሲሆን፣ ጥቂት ጊዜ ሊፈጅ ይችላል። ይህንን ለማድረግ ጀርመን አገር የሚገኘው ይህንን ጉዳይ የሚመለከተው የመንግስት መስሪያቤት መስማማት አለበት።

የዳብሊን ሂደት (Dublin-Verfahren) ማለት ምን ማለት ነው?

እዚህ ከመግባታችሁ በፊት ሌላ የአውሮፓ አንድነት አገር Europäische Union(EU) ነበራችሁ ወይ?
እዚያ የእጅ አሻራ መስጠት ነበረባችሁ ወይ?
ሌላ አገር የጥገኝነት ማመልከቻ አስገብታችኋል?
ጀርመን አገር ከመጣችሁ ምናልባት የተለያዩ የጀርመን መንግስት መስሪያቤቶች አሻራ ስጡ ይሏችሁ ይሆናል። አሻራውን ኮምፒውተር ውስጥ ካለው የሌላ ሰዎች አሻራ ከተጠራቀመበት ጋር ያስተያያሉ። አሻራውን ካገኙ ሌላ የአውሮፓ አንድነት አገር እንደነበራችሁና እዚያም የጥገኝነት ማመልከቻ አስገብታችሁ እንደሆን ማየት ይቻላል።
ጀርመን የአውሮፓው አንድነት(EU) አገር አባል ነች። በአውሮፓ አንድነት አገሮች በሙሉ አንድ ህግ አለ፤ ይኸውም የደብሊን ስርዓት (Dublin Verordnung) በመባል ይታወቃል። በህጉም መሰረት አንድ ጥገኝነትን ያመለከተ ስደተኛ ሰው የት አገር መቆየት እንዳለበት ይደነግጋል። ለአቅመአዳም/ለአቅመሄዋን የደረሱ ሰዎች አልፈው በመጡበት የአውሮፓው አንድነት አገር ተመልሰው መሄድ አለባቸው። ይህ ጉዳይ ግን ዕድሜያቸው ከ18 ዐመት በታች የሆኑ፣ ብቻቸውን የመጡትና (unbegleitete minderjährige) እንዲሁም እዚህ ጥገኝነት ለጠየቁት አይመለከትም።



የትምህርት ዕቅድ ስእላዊ መግለጫ
መሰረተ-ትምህርት (Grundschule)
4/6 ለሁሉም ተማሪ ግዴታ ነው
schule
9 ዓመት
schule
ሁለተኛ ደረጃ
Hauptschule
10 ዓመት
schule
ሁለተኛ ደረጃ
Realschule
12 ወይም 13 ዓመት
schule
ከፍተኛ ደረጃ
Gymnasium
9-13 ዓመት
schule
አጠቃላይ ትምህርት
Gesamtschule
+
+
=
Hauptschulabschluss
Realschulabschluss
Abitur
ለአንድ አንድ የሞያ ትምህርት የሚበቃ
ለብዙ የሞያ ትምህርት የሚበቃ
ሁሉም የሞያ ትምህርት የሚበቃ እና የዩንቨርስቲ ማስገቢያ ፈተና

ትምህርት
አሁን አንድ ነገር መማር

ጀርመን አገር ለወደፊት ዋስትና ያለው ሂወት ለመኖር ትምህርትቤት ገብቶ መማርና የሞያ ስልጠና መውሰድ በጣም አስፈላጊው እርምጃ ነው። እያንዳንዱ የጀርመን ክፍለ-ሃገር የራሱ የሆነ የትምህርት ህግ ሳለለው የትምህርት ዕቅዱ/ስርዓቱ ትንሽ የተወሳሰበ ወይም አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ ስለሚኖራችሁ ዕድልና አማራጭ የተለያዩ ሰዎችን መጠየቅ፣ በተለይም አስተማሪዎቻችሁን፣ ወይም ደግሞ ሞግዚቶቻችሁን መጠየቅ ያስፈልጋል። ከእነሱ ጋር በመሆን የትኛው የትምህርት ዐይነትና ትምህርትቤት ለእናንተ እንደሚስማማ ማወቅ ይቻላል።

ጀርመን አገር ሁሉም ልጆች ትምህርትቤት የመሄድ ግዴታ አለባቸው (Schulpflicht)፤ ይህም ማለት ትምህርትቤት ለመሄድ መብትና ግዴታ አላቸው ማለት ነው። ለትምህርትቤት አይከፈልም። የተለያዩ የትምህርት ዐይነቶች አሉ። መጀመሪያ ሁሉም ልጆች መሰረተ-ትምህርት ቤት ሄደው ይማራሉ። ከዚያ በኋላ ወደሚቀጥለው ትምህርትቤት ይሄዳሉ። ይህም እንደ እያንዳንዱ የጀርመን ክፍለ-ሃገር የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ የትምህርት ዐይነቱም እንደሚከተለው ይከፋፈላል፤ Hauptschule, Realschule, Gymnasium, Integrierte Sekundarschule und Gesamtschule.

የትኛው የሚቀጥለው ትምህርትቤት መግባት እንደምትችሉ የሚወሰነው ትምህርትቤት ባላችሁ ትጋትና በውጤታችሁ ነው። ከአስተማሪዎቻችሁ፣ ከወጣት ተቋሙና ከሞግዚቶቻችሁ ጋር በመሆን የትኛው ትምህርትቤት መግባት እንደሚኖርባችሁ መወሰን ትችላላችሁ

በአንድ ሞያ ለመሰልጠን የግዴታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት „Hauptschulabschluss“ ወይም „Realschulabschluss“ ያስፈልጋችኋል። የትኛው አስፈላጊ እንደሆነ እንደየሞያው ዐይነት ይለያያል። ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ለመማር የግዴታ የ12/13ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ማለት ማትሪክ ያስፈልጋል። Fachabitur የሚባል በተወሰኑ የትምህት ዓይነቶች ብቻ ማትሪክ መፍተን የምያስችልም አለ። ከዛ ብኋላ በተወሰኑ ኮሌጅ ውስጥ ገብታችሁ መማር ትችላላችሁ። ትምህርት ላይ እያላችሁ ልምምድ (Praktikum) ማድረግ ትችላላችሁ። ልምምድ ማድረግ ጥሩ ነው፥ አንድን ሞያ የበለጠ ለማወቅ ይጠቅማል። የትምህርትቤት ልምምድ ለማድረግ ፈቃድ አያስፈልግም። ጀርመን አገር የተለያዩ ልምምዶች ወይም ከሞያ ጋር የሚያያዙ ተግባራዊ ስልጠናዎች ይሰጣሉ። ለአብዛኛዎቹ ከስራ ማእከን እና ከኢሚግሬሽን ቢሮ ፈቃድ ያስፈልጋል።

አሁኑኑ ትምህርት ቤት መግባት እንችላለን?

ሌላ ነገር ከማድረጋችሁ በፊት የግዴታ የጀርመንኛ ቋንቋ መማር አለባችሁ። ዕድሜያችሁ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ በአካባቢያችሁ የሚገኙ ወጣቶችን ማስተማሪያ ልዩ ትምህርትቤት እንድትገቡ ይደረጋል። የመማሪያ ክፍሎች የተለያየ ስም አላቸው፤ ለምሳሌ የእንኳን በሰላም መጣችሁ ክፍል፣የማዋሃድ ክፍልና የጥገኞች ክፍል። የጀርመንኛ ቋንቋ በደንብ መናገር ከጀመራችሁ ማንኛውም ልጅ ገብቶ የሚማርበት ትምህርትቤት መለወጥ ትችላላችሁ። አብዛኛውን ጊዜ ማንኛውም ልጅ ገብቶ የሚማርበት ትምህርት ቤት እንድትገቡ ሲደረግ፣ በተጨማሪ የጀርመንኛ ቋንቋ ትማራላችሁ።

የሞያ ትምህርት ማለት ምን ማለት ነው? እሱንስ ማድረግ እንችላለን?

ትምህርት ቤት መሄድ አስጠልቷችኋል? ወደፊት መስራት እንድትችሉና ደህና ገንዘብ እንድታገኙ የሞያ ስልጠና ተማሩ። ካለሞያ ስራ ፈልጎ ማግኘት በጣም ያስቸግራል።

አንድን ስራ በደንብ ለመማር የቀለም እና ተግባራዊ ይዘቱን መማር ግዴታ ነው። ከሁለት ወይም ሦስት ዓመት ብኋላ በቀለም እና በተግባራዊ ስራ የተማራችሁትን ለማሳየት ትፈተናላችሁ።

ከወጣቶች ተቋም፣ ከሞግዚቶቻችሁ እና ከተንከባካቢዎቻችሁ ጋር የሞያ ስልጠና ትምህርታችሁ ዕቅድ አውጥታችሁ ስላለው አማራጭ ተነጋገሩ። በተጨማሪ በቂ የነጻ ምክርቤቶች ለእናንተ የሚስማማ ሞያ በማፈላለግ ሊረዷችሁ ይችላሉ።

በትምህርትቤትና በፋብሪካዎች ውስጥ የሚሰጥ የሞያ ስልጠና አለ። ከየትም አገር መጣችሁ ጀርመን አገር ብዙ ጊዜም ብትኖሩና የትኛውም ዐይነት የመኖሪያ ፈቃድ ቢኖራችሁም በትምህርትቤት የሚሰጠውን የሞያ ስልጠና ማድረግ ትችላላችሁ።

በፋብሪካ ውስጥ የሚሰጠው የሞያ ስልጠና ከፍተኛ ተግባራዊ መልክ አለው፤ ለመሰልጠን የግዴታ ከኢሚግሬሽን ቢሮ የስራ ፈቃድ („Erwerbstätigkeit gestattet") ማግኘት አለባችሁ።
ማስጠንቀቂያ፤ አገራችሁ ያለስጋት መኖር የሚቻልበት አገር „sicheres Herkunftsland" ነው ተብሎ ከተደነገገ፣ የጥገኝነት ማመልከቻ ብታስገቡም ወይም ማመልከቻችሁ ተቀባይነት ባያገኝም በመሰረቱ በፋብሪካ ውስጥ የሚሰጠውን የሞያ ስልጠና ማድረግ አይፈቀድላችሁም።

የመኖሪያ ዐይነት	የትምህርትቤት ውስጥ ስልጠና	የፋብሪካ ውስጥ ስልጠና
Aufenthaltsgestattung	✓	የሚወስነው የኢሚግሬሽን ቢሮ ነው
Duldung	✓	የሚወስነው የኢሚግሬሽን ቢሮ ነው
Aufenthaltserlaubnis	✓	✓

Abitur ማለት ምን ማለት ነው? ማን ነው ለመማር የሚፈቀድለት?

ለመማር ፍላጎት አላችሁ፣ የሞያ ስልጠና ለማድረግ ወይም ተቀጥሮ ለመስራት ፍላጎት የላችሁም? ለመማር ፍላጎት ካላችሁ ቀጥሉበት!

እስከ አስራሁለተኛ ወይም እስከ አስራሶስተኛ ክፍል ድረስ መማር ትችላላችሁ፤ ከዚያም የመልቀቂያ ፈተና/ማትሪክ ካለፋችሁ ዩኒቨርሲቲ ገብታችሁ መማር ትችላላችሁ። ዩኒቨርሲቲ ገብታችሁ መማርን የሚወስነው ባላችሁ የመኖሪያ ፈቃድ ዐይነትና፣ የትኛው የጀርመን ክፍለ-ሃገር እንደምትኖሩ ነው። ለመማር ከፈለጋችሁ ምክር የሚሰጥበት ቦታ መፈለግ አለባችሁ።

ዕድሜያችን ከ18 ዓመት በታች ከሆነ መስራት ይፈቀድልናል?

አዎ፣ ይህ የሚቻለው ግን የተወሰነ ቅድመ-ሁኔታ ሲሟላ ብቻ ነው። ይህንን በሚመለከት ከተንከባካቢያችሁ ጋር መነጋገር ያስፈልጋል። በተጨማሪም ለወጣቶች ተቋማት መናገር አለባችሁ። ከወጣቶች ተቋማት ገንዘብ የሚሰጣችሁ ከሆነ ከደሞዛችሁ የተወሰነውን ብቻ ለራሳችሁ አስቀርታችሁ ቀሪውን ለወጣቶች ተቋማት መመለስ አለባችሁ። ገንዘቡን ለመመለስ የትኛውም ዐይነት ስራ ቢሆን ወሳኝ አይደለም፤ ለምሳሌ ተጨማሪ ወይም የዕረፍት ጊዜ ስራም ቢሆን (Nebenjob, Ferienjob,...) መመለስ ግዴታ ነው። ገንዘቡን ለወጣቶች ተቋማት መመለስ የማያስፈልገው በፈቃደኝነት ለመርዳት የምትሰሩ ከሆነና ለዚህ ስራ የተወሰነ ገንዘብ ብቻ የሚከፈላችሁ ከሆነ ከሆነ ነው።

ማስጠንቀቂያ፤ ሳይመዘገቡ መስራት ጀርመን አገር በህግ የተከለከና የሚያስቀጣም ነው።

የሞያ ስልጠና ለማድረግም ሆነ ዩንቨርስቲ ለመማር ገንዘብ እንዴት ነው መክፈል የምንችለው

ለወጣቶች የሚደረገው ዕርዳታ ካለቀ፣ የሚቀጥለው ጥያቄ ለመኖር የሚያስፈልገንን ገንዘብ የት ማግኘት እንችላለን? ፋብሪካ ውስጥ የሙያ ስልጠና የምታደርጉ ከሆነ ከማስልጠኛው ቦታ ገንዘብ ይሰጣችኋል። (Ausbildungsvergütung)

ትምህርታችሁን የምትቀጥሉ ከሆነ፣ በትምህርት ቤትም ሆነ በፋብሪካ ውስጥ ስልጠና የምታደርጉ ወይም ደግሞ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የምትማሩ ከሆነ ከዕርዳታ መስጫ(Sozialamt) ቦታም ሆነ ከስራ ማዕከል መስሪያቤት (Jobcenter) ገንዘብ አይሰጣችሁም። ለዚህ ተጨማሪ መረጃ ታች ሰፍሯል። በዚህም ምክንያት የተነሳ የተማሪዎች የመማሪያ ገንዘብ (ክፍያ) (BAföG) ወይም የሞያ ስልጠና ዕርዳታ (Berufsausbildungshilfe BAB) ግዴታ ያስፈልጋል። ይህም ሊወሰን የሚችለው ባላችሁ የመኖሪያ ፈቃድ ዐይነት እና ስንት ዐመት ጀርመን አገር እንደኖራችሁ ታይቶ ነው። ላይ የተጠቀሱት የዕርዳታ ዓይነቶች ይመለከታችሁ እንደሆን ወይም ሌላ አማራጭ ካለ ለማጣራት የሚያማክራችሁ ቦታ መፈለግ አለባችሁ። የተማሪዎች የመማሪያ ገንዘብ/ክፍያ (BaföG) ወይም የሞያ ስልጠና ዕርዳታ (BAB) የምታገኙ ከሆነና፣ በተጨማሪ መስራት ይፈቀድላችሁ እንደሆን መጠየቅ ይኖርባችኋል።

ገንዘቡ የማይበቃን ከሆነ ምን ማድረግ እንችላለን?

ለወጣቶች የሚደረግ ዕርዳታ የማይሰጣችሁ ከሆነና፣ የሞያ ስልጠና ዕርዳታው ወጪችሁን በሙሉ የማይሸፍን ከሆነ ምናልባት ከስራ ማዕከል መስሪያቤት ወይም ደግሞ ከዕርዳታ መስጫ ቦታ ድጋፍ ልታገኙ ትችላላችሁ። ለዚህ ደግሞ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳላችሁ የሚያሳይ ማመልከቻ ማስገባት ያስፈልጋል። ምን ምን ነገሮች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባችሁ መረጃ ጠይቁ።

የስራ ማዕከል (Jobcenter) ምንድነው?

የስራ ማዕከል የመንግስት መስሪያቤት አካል ሲሆን በማንኛውም የጀርመን ከተማና ወረዳ ውስጥ ይገኛል። የስራ ማዕከል ስራ ለሚፈልጉ ለአቅመ ኣዳም/ኣቅመ ሄዋን ለደረሱ ሰዎችን የስራ ቦታ እስኪያገኙ ድረስ ይረዳቸዋል። ኑሮአቸውን ለመደጎም ገንዘብ ይሰጣቸዋል፣ የስራ ቦታም በመፈለግ ያግዛቸዋል። አስፈላጊ ወይም አስቸጋሪ ሁኔታ (Härtefällen) ውስጥ ለሚገኙና ትምህርትቤት ለሚሄዱ ወይም የሞያ ስልጠና ለምያደርጉ ሰዎች የኑሮ ወጪያቸውን ይሸፍንላቸዋል።

የስራ ማዕከል የቤት ኪራይ፣ የምግብና የሕክምና ኢንሹራንስ ይከፍላል። የስራ ማዕክል የሚረዳችሁ ዕድሜያችሁ ከ18 ዓመት በላይ ከሆነና የመኖሪያ ፈቃድ ካላችሁ።

የማህበራዊ ድጋፍ መስጫ መስሪያቤት ምንድነው ?

የማህበራዊ ድጋፍ መስጫ መስርያቤት የመንግስት መስሪያቤት አካል ነው። የወጣት ዕርዳታ የማታገኙ ከሆነ፣ ተቀጥራችሁ የማትሰሩና ምንም ገቢ ከሌላችሁ፣ ከስራ ማዕከልም ምንም ገንዘብ የማታጋኙ ከሆነ የማህበራዊ ድጋፍ መስሪያቤት ይረዳችኋል። የማህበራዊ ድጋፍ መስሪያቤት ለቤት ኪራይ፣ ለምግብና ለሕክምና ኢንሹራንስ ይከፍልላችኋል። የማህበራዊ ድጋፍ መስጫ መስሪያቤት የሚረዳችሁ ዕድሜያችሁ ከ18 ዓመት በላይ ከሆነ፣ የጥገኝነት ማመልከቻችሁ ውሳኔ ካለገኘ፣ ማመልከቻችሁ ተቀባይነት ካላገኘ ወይም ደግሞ “Duldung“ ካላችሁ ነው።

ኖውሃይላ (Nouhaila) 20 ዓመት ከሞሮኮ

ሃቫ ሞሪና (Hava Morina)፥ 16 ዓመት ከኮሶቮያ

ኢክባል ጣርቅ (Iqbal Tariq) 17 ዓመት ከፓኪስታን

ግሆላም ራሱል ሃኪሚ, ሃዛራ (Gholam Rasool Hakimi, Hazara) ከ19 ዓመት በላይ ከአፍጋኒስታን

አይሽ (Aish) 17 ዓመት ከፓኪስታን

አር ምሃንዱ (R. Mhandu) 22 ዓመት

አሊረዛ ሁሴን (Alireza Hossein) ከጋዝኒ አፍጋኒስታን፣ 18 ዓመቴ ነው

ዋኤል ዛርዳህ (Wael Zardah) 16 ዓመት ከደማስቆ

ሶልታን አክባሪ (Soltan Akbari)፣ ሃዛራ (Hazara) ከአፍጋኒስታን፣
የአስራሶስተኛ ክፍል ተማሪ፣ የሚኖረው በርሊን

የባንክ ሂሳብ መክፈት ይፈቀድልናልን?

ጀርመን አገር የሚኖር ማንኛውም ሰው የባንክ ሂሳብ መክፈት ይችላል። ባንኮችም ማንኛውም ሰው የባንክ ሂሳብ እንዲኖረው ይፈቅዳሉ። ጥገኝነት የጠየቁም ሆነ፣ ለግዜው እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው ሰዎች የባንክ ሂሳብ መክፈት ይችላሉ። የባንክ ሂሳብ ጥሩ ነገር ነው፤ ብዙ ስራን ያቀላል። የባንክ ሂሳባችሁ ላይ ግን ገንዘብ መኖር አለበት። በቂ ገንዘብ ባንክ ሂሳባችሁ ውስጥ ሳይኖር አንድ ነገር ከገዛችሁ ወይም ከከፈላችሁ ብዙ ቀረጥ መክፈል ሊኖርባችሁ ይችላል።

በትርፍ ጊዜያችን ምን ማድረግ እንችላለን?

ጀርመን አገር በዕረፍት ጊዜ ብዙ ነገሮችን ማድረግ ይቻላል።
ሃቫ ከዚህ በታች ስለምታካሂዳቸው ልዩ ልዩ ነገሮችና ዕቅዶች ገልጻለች።

„ማንም ሰው የፈለገውን ነገር ማድረግ ይችላል። የእግር ኳስና ቲያትር መጫወት እውዳለሁኝ። ከስፖርት ጋር የተያያዘ ነገር ሁሉ በጣም ደስ ይለኛል። ባለፈው የትምህርት ዓመት ከትምህርት በኋላ በሳምንት ሁለት ጊዜ የእግር ኳስ ጨዋታ ልምምድ Moabiter FSV የሚባለው ቡድን ጋር ሳደርግ፣ ከዚህ በተጨማሪም Clara Out-reach ጋር ተለያዩ የቲያትር ተዋናይነት ልምምድ አድርጌአለሁ። በውጣቶች ፕሮጀክት „Alice im Wunderland“ የ Gangway e.V. የቲያትር ተዋናይነት ላይ (Jugendtheaterfestival FESTIWALLA) በወጣቶች የቲያትር ቢሮ በ2016 ዓ.ም በተዘጋጀው ላይ ተሳትፌአለሁ። ሁከፓክ (HUCKEPACK) የሚባለው ድርጅት ውስጥም በመመዝገብ እኔን በግል የሚረዱኝ ሰዎች ኣግኝቻለሁኝ። እንደ የግል ረዳቴ ሆና ከምትንከባከበኝ ጋር በሳምንት አንድ ጊዜ በመገናኘት ከምኖርበት ቦታ ውጭ በብስክሌት ወጣ ብለን እንሄዳለን፤ ሲኒማ ቤትም እንሄዳለን። እንደዚሁ እንደ የግል ረዳት ሆነው ልጆችን የሚንከባከቡ ሌሎች ድርጅቶችም አሉ። በእርግጥ በምትኖሩበት አካባቢም ተመሳሳይ ድርጅቶች ይኖራል!“

ለእለታዊ ኑሮ የሚሆን መመሪያ

መጓዝ እንችላለን ?

የጥገኝነት ሂደት እየትካሄደ ወይም በ Duldung እየኖራችሁ ካለችሁበት አካባቢ ወደ ሌላ አገር ወይም ከተማ መሄድ አትችሉም። ዘመድ ለመጎብኘት ወይም ከተማሪዎች ጋር ጉዞ ለማድረግ ከፈለጋችሁ፡ ያላችሁ የመኖርያ ፈቃድ ለተወሰነ ቦታ ያገለግል እንደሆንና ከወጣችሁ ስንት ጊዜ መቆየት እንደምትችሉ ማረግገጥ አለባችሁ። ጀርመን አገር ከገባችሁ ጀምሮ እስከ ሶስተኛው ወር ድረስ ካለችሁበት ከተማ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ አብዛኛውን ጊዜ ችግር አለ። ከጀርመን ውጭ ለመሄድ የግዴታ ከኢሚግሬሽን ቢሮ ፈቃድ ያስፈልጋችኋል።

ወደ ውጭ ለመውጣት ፈቃድ ለማግኘት ወይም ካላችሁበት ቦታ እዚሁ ጀርመን አገር እንዳትንቀሳቀሱ የተደረገው ገደብ እንዲነሳ ሞግዚቶቻችሁ የኢሚግሬሽን ቢሮ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ።
የኢሚግሬሽን ቢሮ ብቻውን ውሳኔ ይሰጣል፣ ወይም ደግሞ የመኖሪያ ፈቃዳችሁ Aufenthaltgestatung ከሆነ ደግሞ ክፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ቢሮ ጋር በመተባበ ይወስናሉ።

ብቻችንን ቤት ተከራይተን መኖር እንችላለን?

እንደሁኔታው ነው የሚወሰነው። የራሳችሁን ህይወት በደንብ ለማቀናጀት የምትችሉ ከሆነ ዕርዳታ ለማቀድ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ መጠየቅ ትችላላችሁ። ቤት ለማግኘት ግን ብዙ ግዜ የሚፈጅ ነገር ነው።

መኪና መንዳት ይፈቀድልናል ወይ?

መኪና ለመንዳት የመንጃ ፈቃድ ያስፈልጋል። የመንጃ ፈቃድ አስፈላጊ ቢሆንም ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም። ዕድሜው 18 ዓመት የሞላው ማንኛውም ሰው የመንጃ ፈቃድ ማስወጣት ይችላል፤ ሆኖም ግን ማረጋገጫ መታወቂያ ያስፈልጋሉ።

የመኖሪያ ፈቃድ የትውልድ ሰርተፊኬት ወይም ፓስፖርት ማቅረብ እስካልተቻለ ድረስ የመንጃ ፈቃድ ፈተና ማድረግ አይፈቀድም። የመንጃ ፈቃድ ለማውጣት የጽሁፍና የተግባራዊ ፈተናዎች አሉ። ከዚህም በላይ ብዙ ገንዘብ ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም የመንጃ ፈቃድ ብዝ ገንዘብ ነው የምያስከፍለው።

ዕርዳታ የት ነው የምናገኘው?

የጥገኝነት ማመልከቻ ሂደትና መኖሪያ ስለጥገኝነት ማመልከቻችሁ ሁኔታ ምክር ይሰጧችኋል። እዚያ አጠቃላይ ነገሮች ግልጽ እንዲሆንላችሁ መጠየቅ ወይም ደግሞ ስለተፈጸሙት ነገሮችን፣ ለምሳሌ ስለሰጣችሁት ቃለ-መጠይቅ የተጻፈው ፕርቶኮላችሁ መነጋገር ትችላለሁ። በአብዛኞዎቹ ከተማዎች እንደዚህ ዐይነት የማማከሪያ ቢሮዎች አሉ። ተንከባካቢዎቻችሁ፣ ወይም ደግሞ ሞግዚቶቻችሁ የማማከሪያ ቢሮ የምትኖርበት አካባቢ የት እንደሚገኝ ሊነግሯችሁ ይችላሉ።

ጠበቃ ጠበቃዎች ያስፈልጉናል ወይ?

ጠበቃ የምያስፈልገው ለምሳሌ ስለጥገኝነት ጉዳይ፣ ፍርድቤት ወይም ፖሊስ ጋር መቅረብ ካለባችሁ ወይም ደግሞ ዓመጽ ከገጠማችሁ ነው።

ጠበቃ ምን ማድረግ ይችላል?

ጠበቃ እናንተን የመንግስት ሰራተኞች ጋር፣ ለምሳሌ የፌደራል የኢመግረሽንና የስደተኞች ቢሮ (BAMF)፣ የኢሚግሬሽን ቢሮ ወይም ደግሞ የስራ ማዕከል (JobCenter) ይወክላል። መብታችሁ እንዲጠበቅላችሁ ጠበቃዎቹ ይረዷችኋል። አንድ ሰው ከጎዳችሁ ጠበቃዎቻችሁ ሊከሱ ይችላሉ። ጠበቃዎቻችሁ ለደብዳቤዎቻችሁ መልስ ይሰጣሉ፣ ወይም ክስ ይመሰርቱላችኋል። አንድ መጥፎ ነገር ካጋጠማችሁ፣ ለምሳሌ መጥፎ ደብዳቤ ከመጣ ወይም ደግሞ እንድትባረሩ የሚገልጽ ደብዳቤ ከመጣ ይከራከሩላችኋል። ቃለ-መጠይቅ በሚደረግበት ጊዜም አብሯችሁ ይሄዳሉ።

ማን ነው የጠበቃ ወጪን የሚከፍለው?

በመሰረቱ እናንተ ናችሁ የጠበቃ ዋጋ መክፈል ያለባችሁ፤ ይሁንና ለወጣቶች ዕርዳታ የሚደረግበት ጊዜ አለ። ይህንን በሚመለከት ከሞግዚቶቻችሁ ጋር መነጋገር ያስፈልጋል። ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑና ጥቂት ገንዘብ ላላቸውም ዕርዳታ ይደረግላቸዋል። ይህንንም በሚመለከት ከጠበቃችሁ ጋር መነጋገር ያስፈልጋል።

ጠበቃ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

ሞግዚቶቻችሁን፣ ተንከባካቢዎቻችሁን፣ ጓደኞቻቹን፣ ዘመዶቻችሁን ወይም ደግሞ ምክር መስጫ ቦታ መጠየቅ ይቻላል።

አድልዎ፤

በእናንተም ላይ ሆነ በአካባቢው በሚገኙ ሰዎች ላይ አድልዎ ሊደርስባችሁ ይችል ይሆናል። አንድም ሰው ሆነ ብዙ ሰዎች ማግኘት የሚገባቸውን ነገር እንዳያገኙ የሚደረግ ከሆነ ይህ አድልዎ ነው። አድልዎ በተለያየ መልክ ይገለጻል። በተለይም አንዳንድ ሰዎች በጾታቸው፣ በሃይማኖታቸው፣ በቆዳቸው ቀለምና በዘራቸው፣ እንዲሁም በወሲባዊ ባህርያቸው የተነሳ አድልዎ ይደረግባቸዋል።

በመሰረቱ ጀርመን አገር አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ቢሆንም አልፎ አልፎ ይከሰታል። አድልዎን ዝም ብሎ መቀበል የለባችሁም። አድልዎ ከተፈጸመባችሁ በተቻለ መጠን ለምታምኗቸው ሰዎችም ሆነ አማካሪ ቦታ መናገር ያስፈልጋል፤ ከእነሱ ድጋፍ ማግኘት ይቻላል።

አመጽ ካጋጠማችሁ የሚሰጥ ዕርዳታ፤

ማንም ሰው ቢሆን እናንተን የመጉዳትም ሆነ አደጋ ውስጥ ሊጥላችሁ የሚችል ነገር እንድትፈጽሙ የማስገደድ መብት የለውም። የተለያየ የአመጽም ሆነ የግዳጅ ዐይነት አለ፤ ለምሳሌ ወጣት ወንዶችም ሆነ ሴቶች ትምህርት ቤት ከመሄድ ይልቅ ለሌላ ሰው እንዲሰርቁ፣ እንዲለምኑ፣ ዕፅ እንዲገዙ ይገደዳሉ፣ በወሲብ ስራ ላይ እንዲሰማሩም ሆነ ወይም ሌላ ስራ እንዲሰሩ ይገደዳሉ። ብዙ ሴት ልጆችም ሆነ ወጣት ወንዶች ይደበደባሉ፤ ሌሎች ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው ግልምጫ ወይም ማስፈራሪያ ይደርስባቸዋል። እንደዚሁም አንዳንድ ወጣት ልጆች ደግሞ ወሲባዊ አመጽ ይፈጸምባቸዋል። ይህንን ዐይነቱን አጸያፊ ድርጊት የሚፈጽሙት ዝምድና የሌላቸውም ሆነ ዝምድና ያላቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ብቻችሁን አይደላችሁም! ማስፈራሪያና ክትትል የሚደረግባችሁ ከሆነ ሊረዱ የሚችሉ ማማከሪያና፣ ሲያስፈልግም መጠጊያ ቦታዎች አሉ። የምክር መስጫ ቦታዎች ሊረዷችሁ ይችላሉ። ስለ ጓደኞቻችሁ ብታስቡ እነዚህ የምክር መስጫ ቦታዎች ሊረዷችሁ ይችላሉ።

አንድ የምታምኑትን ሰው ፈልጉና ስላለባችሁ ገጠመኞችና ያለባችሁን ፍርሃት ንገሩት። እነዚህም ተንከባካቢዎች፣ ሞግዚቶች፣ አስተማሪዎች፣ የማህበራዊ ስራ ሰራተኞች፣ ፖሊስ፣ ጎረቤት፣ ጓደኛ ሊሆኑ ይችላሉ። የሚረዳችሁ ሰው በመጀመሪያ ጉዳያችሁን ከሰማ በኋላ ማማከሪያ ቦታ ይፈልግላችኋል።

በሁሉም ከተማ ማማከሪያ ቦታ አለ። በተጨማሪም በሁሉም የጀርመን ምድር ማን እንደሆኑ ሳይገለጽ ዕርዳታ ለማግኘት ስልክ መደወል ይቻላል። ጥቆማ፤ ዕርዳታም ሆነ መጠጊያ ቦታ ከፈለጋችሁ የወጣቶች ተቋማት መርዳት አለባቸው።

በየአንዳንዱ የጀርመን ክፍለ-ሃገር ዕርዳታ ለማግኘት ስልክ የሚደወልበትም ሆነ ልጆች መጠጊያ ማግኘት የምትችሉበት የልጆች መከላከያ ማእከል አለ።

በሚከተለው ስልክ ወጣት ሴቶችም ሆነ ወንዶች መደወል ይችላሉ፤ 08000 116 016

ለLSBTQI: www.queer-refugees.de

አመጽና ክትትል የአዕምሮ ህመም ሊያስከትሉ ይችላሉ። የአዕምሮ ችግር ካጋጠመ ለስደተኞች የህክምና/ቴራፒ ማእከል በመሄድ ዕርዳታ ሊያገኝ ይችላል። እንደዚህ ዓይነቱ የህክምና/የቲራፒ ማእከል በነጻ አገልግሎት ይሰጣል። የነሱ የመገናኛ አድራሻ እዚህ ማግኘት ይቻላል፤

www.baff-zentren.org

A

[Abschiebeverbot] ከጀርመን አገር አስገድዶ ማስወጣትን/ማባረርን የሚከለክል = ጀርመን እንደዚህ ይላል፤ አገራችሁ ይህን ያህል አደገኛ አይደለም። ይሁንና ዕድሜያችሁ ከ18 ዓመት በታች ስለሆነ፣ ወይም ደግሞ በሽተኛ ስለሆናችሁ በግለሰብ ደረጃም አገራችሁ ዕርዳታ ማግኘት ስለማይቻል መመለስ አትችሉም። ስለሆነም እንዳትባረሩ ይደረጋል። ለጊዜው እዚህ ጀርመን አገር መቆየት ትችላላችሁ።

[Abschiebehindernisse] ከጀርመን አገር አስገድዶ ማስወጣትን/ማባረርን ማሰናክል = ይህ ማለት የመኖሪያ ፈቃድ የላችሁም ማለት ነው። ቢሆንም ለተወሰነ ጊዜ እንዳትባረሩ ይደረግ እና Duldung የሚባለው ይሰጣችኋል

[Ablehnung] ተቀባይነት አለማግኘት = ተቀባይነት አለማግኘት የሚለው በማመልከቻችሁ ላይ የመጀመሪያው አሉታዊ ውሳኔ ነው። ይህንን ውሳኔ ለመቃወም ያላችሁ ጊዜ በጣም አነስተኛ ስለሆነ በአስቸኳይ ጠበቃ ያስፈልጋችኋል።

[Altersschätzung] ዕድሜን መገመት = መታወቂያ ከሌላችሁ ዕድሜያችሁ ላይታመን ይችላል። በዚህም ምክንያት የተነሳ ዕድሜያችሁ ይገመታል ወይም በህክምና መሳሪያ ዕድሜያችሁን ለመገመት ሙከራ ይደረጋል።

[Asyl] ጥገኝነት = በአጠቃላይ ዋስትና ያለበት ቦታ ከአደጋ የምታመልጡበት ቦታ ለምሳሌ ከክትትል የምትድኑበት ማለት ነው። ጥገኝነት ጀርመን አገር ከፍተኛ ቦታ ከሚሰጣቸው አንዱ ህግ ሲሆን፣ በህገ-መንግስቱም ውስጥ ሰፍሯል። በአገሩ የፖለቲካ ክትትል የሚደረግበት ማንኛውም ሰው ጀርመን አገር ጥገኝነት የመጠየቅ መብት አለው። ጥገኝንቱ ተቀባይነት ያገኘ ሰው ሶስት ዐመት ያህል ጀርመን አገር መቆየት ይችላል።

[Asylantrag] የጥገኝነት ማመልከቻ = ማንኛውንም የጀርመን አስተዳደር ለምሳሌ፣ የኢሚግሬሽን ቢሮ ወይም ፖሊስ፣ ጥገኝነት ለማመልከት እንደምትፈልጉ ማሳወቅ ትችላላችሁ። እነሱም ፌደራል የኢመግረሽን እና የስደተኞች ቢሮ (BAMF) የጥገኝነት ማመልከቻ እንድታስገቡ ማደረግ አለባቸው። የጥገኝነት ማመልከቻ ማስገባት ማለትም በጀርመን ህገ-መንግስት ወይም በዓለም አቀፋዊ የመጠጊያ ህግ ደንብ መሰረት ጥገኝነት መጠየቅ እንደምትፈልጉ ማሳወቅ ማለት ነው።

[Asylverfahren] የጥገኝነት ሂደት= ፌደራል የኢመግረሽን እና የስደተኞች ቢሮ (BAMF) የጥገኝነት ማመልከቻ ካስገባችሁ በኋላ ጥገኝነት ታገኙ እንደሆን በደንብ ይጣራና ይወስናል። ይህ ሂደት Asylverfahren በመባል ሲታወቅ፣ ረጅም ጊዜም ሊወስድ ይችላል።

[Aufenthalt] መኖር = በአጠቃላይ መኖር ማለት አንድ ሰው የሚኖርበት ወይም የሚቆይበት ቦታ ነው። ከህግ አንፃር መኖር ማለት አንድ የውጭ አገር ዜጋ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ጀርመን አገር መኖር/መቆየት ይችላል ማለት ነው። የመኖሪያ ፈቃድ በጀርመን የመኖርያ ህግ መሰረት(AufenthG) የሚደነገግና በኢሚግሬሽን ቢሮም የሚሰጥ ፈቃድ ነው።

[Aufenthaltserlaubnis] የመኖሪያ ፈቃድ = የውጭ አገር ዜጋ ጀርመን አገር ለተወሰነ ጊዜ የመኖር መብት እንዳለው የሚያሳይ ፈቃድ ነው።

[Aufenthaltsgesetz (AufenthG)] የመኖር ፈቃድ ህግ= ይህ ህግ ወደ ጀርመን አገር መግባትንና መውጣትን፣ እንዲሁም የወጭ አገር ዜጎች ጀርመን አገር መኖር እንዲችሉ የሚደነግግ ህግ ነው።

[Aufenthaltsgestattung] የመኖሪያ ፈቃድ= የጥገኝነት ማመልከቻ ሂደት እየተካሄደ የሚሰጣችሁ የመኖሪያ ፈቃድ ነው።

[Aufenthaltstitel] የመኖሪያ ፈቃድ = ከኢሚግሬሽን ቢሮ ለውጭ አገር ዜጋ በጽሁፍ መልክ የሚሰጠው የመኖር ፈቃድ የሚያረጋግጥ ወረቀት ነው።

[Ausbildung] የሞያ ስልጠና =ማለት ከሁለት እስከ ሶስት ዓመት ተኩል የሚፈጅ የሞያ ስልጠና ሲሆን፣ በፈለጋችሁት ሞያ መሰልጠን ይቻላል።

B

[Behörden] የመንግስት መስሪያ ቤቶች = ህግን

የጽንሰ-ሃሳብ ወይም የቃላቶች ገለጻ

የምያስፈጽሙ መንግስታዊ አካሎች ናቸው። ለምሳሌ የኢመግረሽን ቢሮ።

[Betreuerin/Betreuer] ተንከብካቢዎች = አዋቂ ሰዎች ሆነው የምትኖርበት ቦታ የሚሰሩ ሰዎች ናቸው። ተንከባካቢዎች ሁልጊዜ እናንተ ጋር የሚሆኑና በእለታዊ ኑሯችሁ የሚረዷችሁ ናቸው። ተንከባካቢዎች ለምሳሌ ወደ ሃኪም ቤት፣ ወደ ግዢና ወደ ሌሎች ቦታዎች አብረው የሚሄዱ ሲሆን፣ ጀርመን አገር ምን እንደሚያስፈልጋችሁ ትምህርት ቤትም ሆነ የቋንቋ ትምህርት የምትማሩ ከሆነ በመፈለግ የሚረዷችሁ ናቸው።

[Bundesland] ክፍለ-ሃገር = ጀርመን 16 ክፍለ-ሃገሮች አሏት። እነዚህ ነፃ የሆኑ መንግስታት ሳይሆኑ፣ የራሳቸው ህግና አስተዳደር ያላቸው ናቸው። ይህም ማለት በአብዛኛው ነገር ላይ ነፃ የሆኑና የራሳቸውንም ጉዳይ የሚወስኑ ናቸው።

BumF ፌደራላዊ ለኣቅመ ኣዳም/ሄዋን ላልደረሱና ብቻቸውን ለመጡ ስደተኞች የሚወክል መንግስታዊ ያልሆነ በህግ የተመዘገበ ማሕበር። ይህ ማህበር ከ18 ዓመት በታች የሚገኙ ስደተኞችን መብታቸውን የሚያስጠብቅ ሲሆን የወጣት ስደተኞች ህይወት እንዲሻሻልና የራሳቸውን ህይወት በደንብ እንዲመሩና እንዲገነቡ የሚረዳ ነው።

የኢንተርነት አድራሻችን፡ www.b-umf.de

Facebook: https://www.facebook.com/bumfev

C

[Clearingverfahren] የማጣራት ሂደት = በማጣራት ሂደት ውስጥ ለኣቅመ ኣዳም/ሄዋን ላልደረሱ ስደተኞች የምያስፈልጓቸው ነገሮች፣ ማግኘት ያለባቸው እርዳታና እንክብካቤ ይደነገጋል። በተጨማሪም የጤንነታችሁን ጉዳይ ይመረመራ። ጀርመን አገርም ሆነ ሌላ የአውሮፓ አንድነት አገር ውስጥ የሚኖር ዘመድ ካላችሁና የትኛውም ትምህርትቤት እንደምትገቡ ይጠና። ከዚህም ባሻገር እንዴት እንደተሰደዳችሁና ለመቆየት የሚኖራችሁ ዕድል ይመረመራል። ሁሉም ነገር ከእናንተ ጋር በመሆን ነው የሚከናወነው። ከላይ በተጠቀሱት መረጃዎች መሰረት የዕርዳታ ዕቅድ „Hilfeplan“ ይዘጋጃል። እዛው ላይ በሙሉ ለወደፊት የሚያስፍል የዕርዳታ ኣሰራር ይጻፋል።

D

[Dolmetscher/in] አስተርጓሚ = ብዙ ቋንቋዎችን የሚናገሩና፣ አስፈለጊ ንግግሮችንና መታወቂያዎችን በምትረዱት ቋንቋ የሚተረጉሙ ናቸው።

[Dublin-Verordnung] የዳብሊን ድንጋጌ = በሁሉም የአውሮፓ አንድነት አገሮች የሚያገለግል ህግ ነው። ይህ ህግ የእናንተ የጥገኝነት ሂደት በየትኛው አገር መጠናቀቅ እንዳለበት ይደነግጋል

[Duldung] መባረር ወይም በግድ ማስወጣቱ ቀርቶ ለጊዜው የሚሰጥ ይመኖርያ ፈቃድ = የመኖሪያ ፈቃድ ከሌላችሁ Duldung ይሰጣችኋል። Duldung የምታገኙት ዕድሜያችሁ ከ18 ዐመት በታች ከሆነ ትምህርት የምትማሩ፣ ወይም የሞያ ስልጠና የምታደርጉ ከሆነ ነው። ትምህርት ወይም የሞያ ስልጠናውን እስካልጨረሳችሁና 18 ዓመት እስካልሞላችሁ ድረስ ወይም ሌላ የመኖሪያ ፈቃድ መብት እስክታኙ ድረስ ወረቀቱ በየጊዜው ሊራዘም ይችላል።

E

[Europäische Union (EU)] የአውሮፓ ሕብረት =28 የኣውሮፓ አገሮች ያቀፈ ሲሆን፣ ወደ 500 ሚሊዮን ኗሪ ህዝቦች ያለበት በአንድ ዐይነት ገንዘብና በጋራ የኣውሮፓ ሕግ በሚወስን ፓርላማ የሚመራ ነው።

F

[Familiengericht] የቤተሰብ ፍርድቤት = ይህ ፍርድቤት የቤተሰብ ጉዳይ የሚወስን ፍርድቤት ነው። ስለ ጀርመን አገር ውስጥ ያለወላጆች የሚኖሩ ልጆችንና ወጣቶች ሁኔታ መከታተልም የቤተሰብ ጉዳይ ነው። የቤተሰብን ጉዳይ የሚመለከተው ፍርድቤት ማመልከቻ ከቀረበለት ከ18 ዐመት በታች የሆኑ ልጆችና ወጣቶች ሞግዚቶች እንዲሰጣቸው ይወስናል። ማንኛውም ሰው ማመልከቻ በቤተሰብ ፍርድቤት ሊያስገባ ይችላል።

[Familienzusammenführung] ቤተሰብን አንድ ላይ ማገናኘት/ማሰባሰብ = 18 ዓመት እስኪሞላችሁ ድረስ ጀርመን አገር ከቤተሰቦቻችሁ ጋር የመኖር መብት አላችሁ። ይህም ማለት ወላጆቻችሁ ከእናንተ ተነጥለው የሚኖሩ ከሆነና እናንተ የመኖሪያ ፈቃድም ካላችሁ ወደ ጀርመን የመምጣትና ከእናንተ ጋር የመኖር መብት አላቸው። ይህ ቤተሰብን አንድ ላይ ማገናኘት/ማሰባሰ ተብሎ ይጠራል። አልፎ አልፎም የቀረበ ዝምድና ያላቸውና፣ ወንድም ወይም እህት ወደ ጀርመን አገር በመምጣት አብረው ሊቀላቀሉ ይችላሉ።

[Flüchtlingsrat] የስደተኞች ምክርቤት = የስደተኞች ምክርቤት በማንኛውም የጀርመን ክፍለ-ሃገር ዋና ከተማ ውስጥ ይገኛል። ምክርቤቱ መንግስታዊ ያልሆነ ሲሆን፣ ለስደተኞች መብት መጠበቅ የቆመና የሚከራከር ነው። የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘትና ስለራስም ሁኔታ ለመወሰን ከዚህ ምክርቤት መረጃዎች፣ የህግ ዕርዳታ፣ ድጋፍና እንዲሁም ምክር ማግኘት ይቻላል። የስደተኞች ምክርቤትና የሌሎችም የምክር መስጫ ቦታዎች የያዘ ዝርዝር በProasyl ኢንተርነት ላይ ማግኘት ይቻላል። www. proasyl. de/beratungsstellen-vor-ort/

[Flüchtlingsschutz] የስደተኞች መጠጊያ = ዓለም አቀፋዊ መጠጊያ የሚለውን ተመልከቱ።

[Frauenarzt/Frauenärztin] የሴቶች ሃኪም = የሴት ሃኪም ሴቶችን ወይንም ልጃገረዶችን ብቻ የሚመለከት በሽታ የምያክም ሀኪም ነው። ሴቶች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የሴቶች ሃኪም ጋር ሄደው መመርመር አለባቸው።

G

[Gemeinschaftsunterkunft für Asylbewerber(GU)] ስደተኞችን አንድ ላይ ማኖሪያ ቦታ = የስደተኞችን መጠለያ ቦታ የጥገኝነት ማመልከቻቸው ገና ውሳኔ ያላገኘና Duldung የተሰጣቸው የሚኖሩበት ቦታ ነው። ከ18 ዐመት በታች ከሆናችሁና ያለቤተሰብ ከመጣችሁ እዚያ መኖር አይፈቀድላችሁም። ይህ ከሆነ የወጣቶች ተቋም የእናንተን ጉዳይ ያስተካክላል።

[Gericht] ፍርድቤት = መንግስታዊ የሆነ ተቋም ሲሆን፣ ህግን የሚመለከት ማንኛውንም ነገር እዚያ ይጣራል። አንድ ልጅ ሞግዚት ይሰጠው እንድሆን ወይም ደግሞ ህግን የሚጥስ ስራ ከተሰራ ወንጀለኛ እስር ቤት መግባቱን የሚወስነው ፍርድቤት ነው። በፍርድቤቱ ውሳኔ የማትስማሙ ከሆነ ከጠበቃችሁ ጋር በመሆንና ፍርድቤት በመሄድ ሌላ ውሳኔ ለማግኘት መጣር ትችላላችሁ።

[Grundgesetz] ሕገ-መንግስት = የጀርመን ሕገ-መንግስት ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ በማሳጠር GG ተብሎ ይጻፋል።

H

[Hilfeplanungsgespräch] የዕርዳታ ዕቅድ ንግግር = የዕርዳታ ዕቅድ ንግግር በየስድስት ወሩ ከተንከባካቢዎቻችሁ ከወጣቶች ተቋም እና ከእናንተም ጋር የሚካሄድ ንግግር ነው። ንግግሩ የሚደረገው እናንተ በምን ዐይነት ሁኔታ እንደምትገኙ ለማወቅና ስለወደፊትም ሁኔታ ለማቀድ እንዳለበት ነው። በንግግሩ ላይ ፍላጎትና ችግሮች ካሏችሁ መናገር ይቻላል።

[humanitärer Status/humanitäre Gründe] ሰብአዊ ሁኔታ፣ ሰብአዊ ምክንያቶች = ለዚህ ምክንያት የሚሆኑት፥ ወላጆቻችሁ በህይወት ከሌሉ፣ ወደ አገራችሁ ብትመለሱ አደጋ ውስጥ ትወድቃላችሁ ተብሎ ከታሰበ ወይም ደግሞ የታመማችሁ ከሆነ ነው። ይህ ከሆነ ጀርመን አገር ለመቆየት የሚያስችል ለግዜው የመኖሪያ ፈቃድ

ይሰጣችኋል። ይሁንና የመኖሪያ ፈቃዱ 18 ዐመት እስኪሞላችሁ ድረስ ብቻ ሊሆን ይችላል።

I

[Identitätspapiere] የመታወቂያ ወረቀት = የመታወቂያ ወረቀት የእናንተን ማንነት የሚያሳይ ሲሆን፣ ስማችሁ ማን እንደሆነ፣ የትና መቼ እንደተወለዳችሁ የሰፈረበት ነው። ይህ ወረቀት ፓስፖርት ወይም ደግሞ የትውልድ ሰርተፊኬት ሊሆን ይችላል።

[Inobhutnahme] ኃላፊነት መውሰድ = ዕድሜያቸው ከ18 ዐመት በታች የሆነና ካለወላጆቻቸው ወይም ካላሳዳጊያቸው ጀርመን አገር የመጡ ልጆችን በሚመለከት ኃላፊነትን የሚወስደው የመንግስት የሆነው የወጣቶች ተቋም ነው። የመንግስት ተቋም እናንተ እርግጠኛ የሆነ ቦታ እንድትኖሩ ማንኛውንም ጥረት ያደርጋል። እዚያም ምግብና ልብስ ሲሰጣችሁ በተጨማሪም የህክምና ዕርዳታና እንዲሁም እንክብካቤ ይደረግላችኋል። ይህ ኃላፊነትን መውሰድ በመባል ይታወቃል።
በመጀመሪያ ወቅት የተወሰነ ቦታ ይሰጣችሁ እንደሆነ ይመረመራል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የወጣቶች ተቋም የእናንተን ሁኔታ ይከታተላል። ይህም ጊዜያዊ ኃላፊነትን መውሰድ በመባል ይታወቃል።

[Integrationskurs] የማዋሃድ ኮርስ = የአንድ ሰው ጥገኝነት ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘና ጀርመን አገር እንዲቆይ ከተፈቀደለት እዚህ አገር ለመኖርና ለመግባባት የግዴታ Integrationskurs የሚባለውን የጀርመንኛ ቋንቋ መማር አለበት። የማዋሃድ ኮርስ አቅመ አዳም/ሄዋን ለደርሱ እና ቋንቋ ለማይችሉ ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ነው።

[Internationaler Schutz] ዓለም አቀፋዊ እንክብካቤ = ዓለም አቀፋዊ እንክብካቤም ጥገኝነት ሲሆን፣ ሊያገለግል የሚችለው በጀርመን ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በአውሮፓ ውስጥ ነው። ዓለም አቀፋዊ እንክብካቤም ከአውሮፓው ህግ ጋር የሚጣጣም ስለሆነ ብስደተኝነት ተቀባይነት ካገኛችሁ ወይም "subsidiären Schutz" ከተሰጣችሁ በጀርመን አገር መኖር ትችላላችሁ። ሁለቱንም ልታገኙ የምትችሉት በአገራችሁ ጦርነት ከተካሄደ ነው።

[Interview im Asylverfahren] በጥገኝነትን ሂደት የሚካሄድ ቃለ-መጠይቅ = የጥገኝነት ማመልከቻ ካስገባችሁ አንድ የፌደራል የኢመግረሽን እና የስደተኞች ቢሮ (BAMF) ሰራተኛ እናንተ ጀርመን ኣገር ጥገኝነት ለማግኘት አስፈላጊውን ነገሮች የምታሟሉ መሆኑን ለማወቅ ቃለ-መጠይቅ ያደርጉላችኋል። ከየት አገር እንደመጣችሁ፣ ስለአገራችሁ ሁኔታና እንዲሁም ማን እንደሆናችሁና እንዴትስ ለማምለጥ እንደቻላችሁ ጥያቄ ይቀርብላችኋል። የጀርመንኛ ቋንቋ የማትችሉ ከሆነ ጥያቄውን የሚተረጉምና መልሱንም የሚያስተላልፍ አስተርጓሚ ይመደባል። ሁሉም ጥያቄዎችና መልሶች በደንብ ይመዘገባሉ። ከቃለ-መጠይቁ በኋላ ቃለ-መጠይቁ ያካሄደው ሰራተኛ የተጠየቃችሁንና የሰጣችኋቸውን መልሶች በሙሉ ያነባል። የሰጣችኋቸውን ወረቀቶች/ዶክመንቶች ይመለከታል። ከዚያ በኋላ ጥገኝነት ማግኘት ትችሉ እንደሆነና፣ ጀርመን መቆየት ትችሉ እንደሆነ ይወስናል።

J

[Jugendhilfe] የወጣቶች ዕርዳታ = የወጣቶት ተቋምና ሌሎች ድርጅቶች ለልጆች የሚሰጡት ማንኛውም ዕርዳታና ድጋፍ ነው። የወጣቶች ተቋም ምን መስራት እንዳለበት እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጋቸው፣ እዚህ የሚኖሩ ልጆች ኑሮአቸው ዋስትና እንዲኖረው እና ጥሩ ስሜትም እንዲኖራቸው በሚመለከተው ህግ ውስጥ በሚገባ ሰፍረዋል[Kinder-und Jugendhilfegesetz (KJHG)]።

[JOG] ወጣቶች ያለገደብ = ወጣቶች ያለገደብ የሚለው ድርጅት በ2005 ዓ.ም በጠቅላላው በጀርመን አገር የሚኖሩ በወጣት ስደተኞች ውህደት የተቋቋመ ድርጅት ነው። መሰረታዊ መነሻችን፥ እኛን የሚመለከት ጉዳይ እኛ ወጣት ስደተኞች የራሳችን ድምጽ ያለን እንጂ በውክልና ፖለቲካ መስራት አንፈልግም የሚል ነው።

እኛው እራሳቸን ምን ዐይነት ውሳኔ እንደምናስተላልፍና ይህንንም እንዴት ተግባራዊ እንደምናድርግ እንወስናለን። ወጣቶች ያለገደብ የሚለው ማህበር ማንኛውንም አድልዎና፣ በተለይም ደግሞ ዘረኝነትን፣ ፋሺዝምንና ፀረ-እስላምና ሃይማኖትን አጥብቆ ይቃወማል። የኛ ኢንተርነ www.jogspace.net, facebook: https://de-de.facebook.com/jogspace

K

[Kinder-und Jugendhilfegesetz (KJHG)] የልጆችንና የወጣቶችን እርዳታ ህግ = የልጆችንና የወጣቶችን እርዳታ የሚመለከት ህግ የተጻፈበት ነው። አንዳንዶች በማሳጠር ኤስጌቤ 8 „SGB VIII“ ብለው ይጠሩታል።

[Klage/Klagen] ክስ/ክሶች = ፍርድ ቤት እንዲያየው የሚቀርብ ነገር ክስ ተብሎ ይጠራል። ለምሳሌ የጥገኝነት ማመልከቻችሁ ተቀባይነት ካላገኘ የተቃውሞ ክስ ማቅረብ ይቻላል። አብዛኛውን ጊዜ እንደዚህ ያለውን ነገር ጠበቃ ጋር በመሆን ነው ይግባኝ ማለት የሚቻለው። እንደዚህ ዐይነት ነገር ሲከሰት በተቻለ መጠን በፍጥነት ማድረግ ያስፈልጋል።

M

[Minderjährige/r] ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ያልደረ = ከ18 ዓመት በታች ያሉ ማንኛቸውም ወጣቶች በዚህ መልክ ይጠራሉ።

O

[Organisation/en] ድርጅት/ድርጅቶች = አንድን ነገር ለመስራት በብዙ ሰዎች ውህደት የትቋቋመ ድርጅት ነው። የብዙ ድርጅቶች አባል በመሆን በትጋት መሳተፍ ይቻላል፤ ለምሳሌ የኳስ ቡድን ድርጅት አባል መሆን ይቻላል። ዋና ዓላማውም ከሌሎች ጋር በመሆን ኳስ ለመጫወት ነው። የአብዛኛው ድርጅቶች አባል ሳይኮ ዕርዳታ የሚገኝበት ጊዜም አለ። ለምሳሌ ወጣት ስደተኞች ከስደተኞች ምክርቤትና ከተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የስደተኞች ዕርዳታ ድርጅት (UN-HCR) ዕርዳታ ማግኘት ይቻላል።

P

[Protokoll] የሃሳብ ምዝገባ = በዚህ መዝገብ ላይ ስትጠየቁ የሰጣችኋቸው ቃሎች በሙሉ ይሰፍራሉ። ዝርዝሩን የያዘው ደብዳቤም ከሰጣችኋቸው ቃሎች ጋር በሙሉ ይመሳሰሉ እንደሆን ለማወዳደር ይላኩላችኋል። የሚላከው በጀርመንኛ ቋንቋ ስለሆነ ሻዜ ሰጥቶ የሚተረጉምላችሁና የሚያስረዳችሁ ሰው ያስፈልጋል።

[Psychologen/Psychotherapeuten] የስነ-ልቦና መርማሪዎችና ሃኪሞች = የሞያ ዘርፍ ሲሆን፣ የስነ-ልቦና ችግር ሲያጋጥማችሁ የሚረዱ ናቸው። እየተደጋገመ የሚመጣ ቅዠት፣ ፍርሃትና መጥፎ አስተሳሰብ የስነ-ልቦና ችግር ምልክት ነው። በስደተኞች ላይ የሚከሰተውን እንደዚህ ዐይነቱን የአዕምሮ ችግር ለማከም የሚረዳ የስደተኞች ማከሚያ ቦታ (Therapiezentren für Flüchtlinge) የሚባል አለ።#

R

[Rechtsanwalt/Rechtsanwältin] ጠበቃ = አንድ ራሱን የቻለ የሞያ ዘርፍ ሲሆን፣ ከህግ ጋር የተያያዘ ችግር ሲያጋጥማችሁ የሚረዱ በፍርድቤትም የሚውክሏችሁ ናቸው።

[Residenzpflicht] የመቆየት ግዴታ = በኢምግሬሽን ቢሮ ከምትኖሩበት ከተማ ውጭ እንዳትንቀሳቀሱ የሚደረግ ገደብ ነው። Duldung ካላችሁ መንቀሳቀስ የምትችሉት በዚያው የኢሚግሬሽን ቢሮ በሚገኝበትና በተመዘገባችሁበት ክፍለ-ሃገር ብቻ ነው። በጠቅላላው ጀርመን አገር ለመንቀሳቀስ ከፈለጋችሁ አካባቢን ለቆ መሄድ የሚያስችል ፈቃድ „Verlassenserlaub-nis“ በኢሚግሬሽን ቢሮ ማመልከት ያስፈልጋል። ይህ ሁልጊዜ የሚቻል አይደለም። ጠበቃችሁ በምትኖሩበት

ከተማ የማይኖሩ ከሆነ፣ ሃኪም ጋር የግዴታ መሄድ ካለባችሁ ወይም ደግሞ ዘመዶቻችሁን ለመጎብኘት ከፈለጋችሁ የኢሚግሬሽን ቢሮ የመንቀሳቀስ ፈቃድ ይሰጣችኋል። የወጣት ተቋሙ የሚረዳችሁ ከሆነ ሞግዚቶቻችሁን እንደዚህ ዐይነት ፈቃድ ሊሰጧችሁ ይችላሉ። ፈቃድ ሳታገኙ ካላችሁበት ቦታ ወደ ሌላ ክፍል-ሀገር ከሄዳችሁና እዚያ ፖሊስ ቢይዟችሁ ወደ ፊት ለመንቀሳቀስ በምትፈልጉበት ጊዜ ፈቃድ ላይሰጣችሁና የገንዘብ ቅጣትም ሊያጋጥማችሁ ይችላል።
የወጣቶች መኖሪያ ቦታ እንድትኖሩ ከተደረገ አንድ ቦታ ብቻ የመቆየት ግዴታ ሊኖር አይችልም። ስለሆነም ከሞግዚቶቻችሁና ከወጣቶች ተቋም ጋር በመሆን የኢሚግሬሽንን ቢሮ መጠየቅ ይቻላል።
[Röntgen(Untersuchung)] በጨረር ምርመራ(ኤክስ ሬይ) = በእንደዚህ ዐይነቱ የህክምና ምርመራ አንደኛው የሰውነት ክፍላችሁ በፀረር አማካይነት ሲታይ፣ አጥንታችሁም ፎቶ ይነሳል።

S

[Subsidiärer Schutz] የዕርዳታ መጠጊያ = ዓለም አቀፋዊ መጠጊያን ተመልከት፤
[Schulabschluss] የትምህርት ማገባደድ = ተማሪዎች የመካከለኛ ደረጃ ፈተናቸው አልፈው ትምህርታቸውን ሲያገባዱ የጽሑፍ ሰርተፊኬት ያገኛሉ።
[Schulpflicht] ትምህርትቤት የመሄድ ግዴታ = በጀርመን አገር 16 ዓመት ያልሞላቸው ልጆች ትምህርት ቤት የመሄድ መብትና ግዴታ አለባቸው። ይህ ትምህርትቤት የመሄድ ግዴታ ይባላል።
[SGB VIII] የማህበራዊ ህገ-መጽሀፍ = ይህ ስምንተኛው ህግ የማህበራዊ መጽሓፍ ነው። ይህ ሕግ ከልጆችና ከወጣቶች የዕርዳታ ህግ ጋር አንድ ዓይነት ነው።
[Sorgeberechtigte/r] ኃላፊነትን የሚወስድ = ኃላፊነትን በመውሰድ 18 ዓመት ያልሞላቸውን ልጆች የሚንከባከቡ ሰዎች ናቸው። አንድን ልጅ በኃላፊነት የሚወስድ ሰው የልጁን ንጽህና ይጠብቃል፤ በደንብ ያሳድገዋል፤ የት እንደሚኖርም ይወስናል።ከዚህም በተጨማሪም ከአደጋ ይከላከልለታል፤ ብፍርድቤትም ይወክለዋል፤ የውል ስምምነትም ይፈርምለታል። ለምሳሌ የሞያ ትምህርት ውል ይፈርምለታል። አብዛኛውን ጊዜ ልጆችን የማሳደግ ኃላፊነት ያለባቸው ወላጆች ናቸው። ይህንን ማድረግ የማይችሉ ከሆነ እንደወላጆች ሆኖ የሚያሳድገው ሞግዚት ሙሉ ኃላፊነትን ይወስዳል።

U

[Unbegleitete minderjährige Ausländer (umA)] ኣቅመ ኣዳም/ሄዋን ሳይሞላቸው ያለወላጅ የመጡ የውጭ አገር ልጆች = ያለወላጆቻቸው የመጡ ዕድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላቸው ስደተኖች ማለት ነው።
[Unbegleitete minderjährige Flüchtlinge(umF)] ኣቅመ ኣዳም/ሄዋን ሳይሞላቸው ያለወላጅ የመጡ ስደተኞች = ይህ 18 ዓመት ያልሞላቸውንና ብቻቸውን በስደት ላይ የሚገኙ ሁሉም በስደት ያሉ ልጆች ያጠቃልላል።
[Unbegleitete Minderjährige (UM)] ኣቅመ ኣዳም/ሄዋን ሳይሞላቸው ያለወላጅ የመጡ= ይህም ተጨማሪ ኣባባል 18 ዓመት ላልሞላቸው ስደተኞች ልጆች ነው።
[UN-KRK] = ዓለም አቀፋዊ ሕግ የሆነና በሁሉም አገሮች የልጆች ተወካዮች ተቀባይነትን ያገኘ የልጆችን ህይወት የሚከላከል ደንብ። በUN-KRK ውስጥ 18 ዐመት ያልሞላቸውን ሁሉንም ልጆች የሚመለከት የሰብአዊ መብት ጥበቃ በደንብ ተጽፏል። UN-KRK ሁሉም የፈረሙ አገሮች ይህንን ደንብ ማክበር መጠበቅ አለባቸው የጀርመንም መንግስት እንደዚሁ ይህንን ህግ ያከብራል።
[Unterbringung] መጠለያ መስጠት = ልጆችንና ወጣቶች በወጣቶች ተቋም እርዳታ የሚያኖርበት ቦታ ነው። እዚያ ቦታ ከሌሎች ልጆች ጋር ስትኖሩ በተንከባካቢዎቻችሁ አማካይነት ማንኛውንም ዕርዳታ ታገኛላችሁ። የተለያየ ዐይነት የመጠለያ ወይም የመኖሪያ ቦታዎች አሉ፤

የወጣቶች መኖሪያ፣ አንድ ላይ በመሆን የሚኖርበት ስፍራ ወይም ደግሞ ለብቻ ተከራይቶ የሚኖርበት ቤት። የትኛው ለእናንተ እንደሚስማማ ከወጣት ተቋም ጋር በመሆን ልትወስኑ ትችላላችሁ።

V

[Volljährigkeit, volljährig] ለአቅመ-አዳም የደረሱ = በአብዛኛዎቹ አገሮችና ጀርመንም አንድ ልጅ 18 ዓመት ከሞላው ዕድሜው ለአቅመ-አዳም ደርሷል ይባላል። በአንዳንድ አገሮች ልጆች ለአቅመ-አዳም የሚደርሱበት ጊዜ ዘግይተው ነው። ለአቅመ-አዳም ስትደርሱ ውል የመዋዋል መብት ኣላችሁ። በተጨማሪም ፍርድቤት ሙሉ ኃላፊነት ትወስዳላችሁ። ለአቅመ-አዳም ስትደርሱ ከዚህ በፊት የነበራችሁን ልዩ ዐይነት የልጆች ድጋፍ ይቀራል ሞግዚቶችም አይኖራችሁም። ሞግዚት የማግኘት መብት የሚውሰነው አገራችሁ ባለው ህግ መሰረት ነው። ይህም ማለት ለአቅመ-አዳም በአገራችሁ ውስጥ ዘግየት ብሎ የሚደረስ ከሆነ እስከዚያ ግዜ ድረስ ሞግዚት ይደረግላችኋል። ምናልባት የአቅመ-አዳም መግቢያ ከ18 ዐመት በታች ከሆነበት አገር ከመጣችሁ፥ ይህ ጀርመን አገር አይሰራም። 18 ዐመት ያልሞላቸው ሁሉም ልጆች ለአቅመ-አዳም እንዳልደረሱ ነው የሚቆጠረው።

[Vormund-Vor-mundin] ሞግዚት = 18 ዓመት እስኪሞላችሁ ድረስና ወላጆቻችሁ እዚህ እስከሌሉ ድረስ ሞግዚቶቻችሁ ኃላፊነቱን ይወስዳሉ። ከሞግዚቶቻችሁ ጋር ለምሳሌ ስለመኖሪያና ስለ ትምህርት ቤት ትነጋገራላችሁ። የሞያ ስልጠና ውልም ሆነ የተንቀሳቃሽ ስልክ ውል የሚፈርሙት ሞግዚቶቻችሁ ናቸው።

W

[Widerspruch] ይግባኝ = እናንተን የሚመለከት ከመንግስት አካል ከሆነው መስሪያቤት የሚመጣ ውሳኔን በጽሁፍ መልክ መቃወም/ይግባኝ ማለት ነው።

[Wohngruppe] አንድ ላይ መኖር = ልጆች በወጣት ተቋም አማካይነት አንድ ላይ እንዲኖሩ ሲደረግና ተንከባካቢዎች ድጋፍ ሲያደርጉላቸው።

Z

[Zeugnis/se] የምስክር ወረቀት = በጣም አስፈላጊ የሆነ በዓመት መጨረሻ ከትምህርት ቤት የሚሰጥ ሰርተፊኬት። በምስክር ወረቀቱ ላይ ሁሉም የትምህርት ዐይነት ውጤቶች፣ ማለትም ጀርመን፣ ሂሳብ፣ እንግሊዘኛ ወዘተ ይሰፍራሉ። ትምህርትቤት ስትቀይሩ ወይም ለስራ ቦታ ስትፈልጉ የምስክር ወረቀት ማሳየት ያስፈልጋል።

አሳታሚ።
Bundesfachverband unbegleitete minderjährige Flüchtlinge e.V.
Paulsenstr. 55 – 56
12163 Berlin
Germany
Email: info@b-umf.de
Telephone : +49 (0)30 82 09 743 – 0
Fax: +49 (0)30 82 09 743 – 9

Jugendliche ohne Grenzen
facebook: /jogspace
twitter: @jogspace
email: jog@jogspace.net
website: jogspace.net

ተባብረው የሰሩ:
ኢክባል ጣርቅ፣ ዋኤል ዛርዳህ፣ ኣር ምሃንዱ፣ አይሽ፣ አሊረዛ ሁሴን፣ ሃቫ ሞሪና፣ ግሆላም ራሱል ሃኪሚ፣ ኖውሃይላ፣ ዊሳም፣ ሶልታን አክባሪ፣ ፍራንሲስካ ሽሚድት፣ ሚርያም ለሸክ እና ጃኒና ሮስት።

ምስጋና ለቶቢያስ ክላውስ እና ኡልሪከ ሽቫርስ ስለ ኣደረጉት እርማት

Design: Kai Noah Schirmer & Ahmed Isam
November 2016

ድጎማ
በSilicon Valley Community Foundation
እና ብግለሰቦች የተሰጠ እርዳታ

ኣንድ ኣንዱ የዚህ መጽሃፍ ክፍል እንኳን በሰላም መጣቹሁ ከሚለው የBUMF ኣንደኛው ክፍል የተሞረከዘ ነው።

ትርጉም:
Übersetzung: Bosena Negussie, Dr. Fekadu Bekele
እርማት:
Amharish Lektorat: : Herr Adhanom, Ruth Gebresllasie
Inhaltliche Prüfung : Almaz Haile

Deutsches Rotes Kreuz

:do Stiftung

Gefördert vom:
Bundesministerium für Familie, Senioren, Frauen und Jugend

www.kommgutan.info

Jugendliche ohne Grenzen

BumF Bundesfachverband unbegleitete minderjährige Flüchtlinge